# Table of Contents


ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 1 ... 4
የአየር ንብረት ለዉጥ ምንነት እና አሉታዊ ተጽኖዎቹ ... 4
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን ... 6
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች ... 6
ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 2 ... 9
የአየር ንብረት ለዉጥ ተግዳሮቶች በኢትዮጵያ ... 9
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን ... 12
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች ... 13
ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 3 ... 14
የአየር ንብረት ለዉጥ መከሰት ዋና ዋና መንስኤዎች ... 14
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን ... 16
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች ... 17
ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 4 ... 18
የአየር ንብረት ለዉጥ የዓለም አቀፍ አጀንዳ ስለመሆኑ የሚየሳዩ ታሪካዊ ዳራዎች ... 18
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን ... 22
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች ... 22
ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 5 ... 24
የደን መመንጠርና መመናመን መንስኤዎች እና ሬድ ፕላስ ... 24
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን ... 27
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች ... 27
ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 6 ... 28
ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) እና የዓለም አቀፍ ጉዳይ የመሆኑ ጽንሰ ሀሳብ ... 28
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን ... 33
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች ... 33
ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 7 ... 35

ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አባል ሀገራት አንዷ የሆነችባቸዉ ምክንያቶች 35

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 38

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 38

ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 8 40

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ዋና ዋና ሰነዶች 40

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 42

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 43

ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 9 44

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) እና ዋና ዋና ሰነዶቹ በኢትዮጵያ የደረሱበት የአተገባበር ደረጃ 44

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 47

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 48

ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 10 49

የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) እና በዋና ዋና ሰነዶች አተገባበር ላይ የሰጠዉ ምላሽ 49

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 51

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 51

ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 11 53

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ትግበራ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎች 53

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 56

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 56

ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 12 58

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ለሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሔዎች 58

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 61

የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 61

ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 13 64

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ ለሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሔዎችን በአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ እንደ ተሞክሮ የመዉሰድ አስፈላጊነት 64
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 68
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 68
ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 14 71
ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ዙሪያ ጥቅም የመጋራት አሰራሮች 71
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 73
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 74
ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 15 76
በዓለም አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የግጭት አፈታት ስርዓቶች 77
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 80
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 80
ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 16 82
በኢትዮጵያ ያሉ የቅሬታ አፈታት አማራጮች 82
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 85
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 85
ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 17 87
በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ትግበራ እና አፈጻጸም ወቅት ሊነሱ የሚችሉ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያገለግሉ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች 87
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን 89
የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች 90
በሬድዮና በቪዲዮ ግንዛቤ ማዳበሪያ ሥራዎቻችን ዙሪያ ነፃ የሕዝብ አስተያየት 91

## ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 1

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**

**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልክቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## የአየር ንብረት ለዉጥ ምንነት እና አሉታዊ ተጽኖዎቹ

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዘሬዉ ፕሮግራም በኂላ፡-

1. የአየር ንብረት ለዉጥ ምንነትን ይገነዘባሉ፤
2. የአየር ንብረት ለዉጥ የሚገለጥባቸዉን ተፈጥሯዊና አካባቢያዊ ክስተቶች ለይተዉ ይረዳሉ፡፡
3. የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተጽዕኖዎች ይገነዘባሉ፡፡

የአየር ንብረት ለዉጥ ምንነት

- ✓ የአየር ንብረት ለዉጥን አስመልክቶ በዓለም ላይ ሁሉም የሚስማማበት ወጥ የሆነ ትርጉም ላይ እስከ አሁን አልተደረሰም፡፡
- ✓ ሆኖም አብዛኞቹ የዘርፉ ባለሙያዎች ቀጥሎ በሚቀርበዉ የአየር ንብረት ለዉጥ ትርጉም ይስማሙበታል፡፡
  - የአየር ንብረት ለዉጥ ማለት ለረዘመ ጊዜ የሚዘልቅ የምድር ከባቢ አየር ለዉጥ ሲሆን፤
  - ይህም የሚከሰተዉ በተለይ በከባቢ አየር ላይ በሚፈጠር የአማካይ ሙቀት መጨመር ምክንያት ነዉ፡፡
  - የአየር ንብረት ለዉጥ የአጭር ጊዜ ለዉጥ ካለመሆኑ የተነሳ በአጭር ጊዜ ምልከታ ሊገለጥ አይችልም፡፡
  - የአየር ንብረት ለዉጥ መኖሩ የሚታወቀዉ የለዉጡ ሂደት ከጀመረ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነዉ፡፡

በእነዚህ አሉታዊ ተጽእኖዎቹ ምክንያት የአየር ንብረት ለዉጥ በአሁኑ ሰዓት ለሰዉ ልጆች ደህነት፣ ለብዝሀ-ሕይወት እና ለአጠቃላይ ልማት ከፍተኛ ስጋት ሆኖ ይታያል፡፡

የአየር ንብረት ለዉጥ መኖሩን እንዴት ልንረዳ እንችላለን?

የአየር ንብረት ለዉጥ መኖሩን በአለም በአጠቃላይ እና በአከባቢያችን በተለይ ከሚስተዋሉ እና ከተከሰቱ እንዲሁም እየተከሰቱ ያሉ የተፈጥሮ አደጋዎችን በመመልከት መረዳት እንችላለን፡፡ በአለም የአየር ንብረት ለዉጥ መኖሩን ከምንረዳባቸዉ ምልክቶች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡ እነሱም፡-

ሀ. በበረዶ አለት በተሸፈኑ አከባቢዎች የበረዶ አለት መቅለጥ እና በዚህም ሳቢያ የዉቅያኖስ እና የባህር ዉኃ ገጽ መጨመር፤

ለ. በዉቅያኖሶች እና በደሴቶች አካባቢዎች በዉኃ ገጽ መጨመር እና ተያያዥ ምክንያቶች የከባድ አዉሎ ንፋስና አደገኛ ማዕበል መከሰት ፣

ሐ. በእነዚህ አደጋዎች ሳቢያ በዉቅያኖስ እና ባህር አከባቢ እና በደሴቶች የሚኖሩ ማህበረሰቦች ሕይወት ጤና እና አጠቃላይ ሕልውና አደጋ ላይ መዉደቅ፡፡

መ. የመሬት መንሸራተት እና አደገኛ ጎርፍ መከሰት እንዲሁም

ሠ. የውኃ እና የየብስ ብዝሀ-ሕይወት መመናመን ፣ በውኃ እና በየብስ የሚኖሩ እንስሳትና እና እፅዋት ምርታማነት መቀነስ ፣ መመረዝ እና መጥፋት ፣ ወዘተ…፡፡

በአካባቢያችን የአየር ንብረት ለዉጥ ከሚገለጥባቸዉ መንገዶች ወይም ተፈጥሯዊና አከባቢያዊ ክስተቶች የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነሱም፡-

ሀ. የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር፤

ለ. ወቅታቸዉን ያልጠበቁ የዝናብ ወራት መታየት፤

ሐ. ተደጋጋሚ የድርቅ መከሰት እና በዚህ እና ተያያዥ ምክንያቶች የሚከሰት በረሃማነት፤

መ. የወንዞችና ምንጮች የወኃ መጠን መቀነስ/መድረቅ፤
ሠ. አደገኛና ደራሽ ጎርፎች በተደጋጋሚ መከሰት እና
ረ. በአግሮ ኢኮሎጂያዊ የአመራረት ዘይቤ ላይ የሚታዩ ለዉጦች መከሰት፡፡

ለምሳሌ፡- በቆላና ወይና ደጋ አካባቢ በመብቀልና በማደግ የሚታወቁ ሰብሎችና እጽዋት በደጋ አካባቢዎች በቅለዉ ማደግ እና በደጋና ቀዝቃዛ አካባቢዎች በመብቀልና በማደግ የሚታወቁ ሰብሎችና እጽዋት ከአካባቢዎቹ መጥፋት ወይም የእነዚህ ዕጽዋትና ሰብሎች የምርት መጠን በዘላቂነት መቀነስ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸው ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡
ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. የአየር ንብረት ለዉጥ ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. በአካባቢያችን አየር ንብረት ለዉጥ ከሚገለጥባቸዉ ተፈጥሯዊና አካባቢያዊ ክስተቶች 3ቱን ጥቀስ/ሽ፡፡
3. ከአየር ንብረት ለዉጥ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ከተከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች ሦስቱን ጥጠቀስ፡፡
4. በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት በደጋማዉ የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ አግሮ ኢኮሎጂያዊ የአመራረት ሥርዓት ላይ ከተከሰቱ አዳዲስ ለውጦች 2ቱን ጥቀስ/ሽ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ1ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

የአየር ንብረት ለዉጥ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ትርጉም የለዉም፡፡ ይሁን እንጂ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች በአብዛኛዉ ጠቅሰዉ የመለሱ መላሾች በትክክል መልሰዋል ማለት ይቻላል፡፡

- የአየር ንብረት ለዉጥ ማለት ለረዘመ ጊዜ የሚዘልቅ የምድር ከባቢ አየር ለዉጥ ነዉ፡፡
- ይህ ለውጥ የሚከሰተውም በተለይ በከባቢ አየር ላይ በሚፈጠር የአማካይ ሙቀት መጨመር ምክንያት ነዉ፡፡
- የአየር ንብረት ለዉጥ የአጭር ጊዜ ለዉጥ ካለመሆኑ የተነሳ በአጭር ጊዜ ምልከታ ሊገለጥ አይችልም፡፡
- የአየር ንብረት ለዉጥ መኖሩ የሚታወቀዉ የለዉጡ ሂደት ከጀመረ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነዉ፡፡

**የ1ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

የ2ኛ ጥያቄ ሙሉ መልሶች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች ከተመለከቱት መልሶች ዉስጥ 3ቱን የመለሰ ተሳታፊ ተሸላሚ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡ መልሶቹም፡-

ሀ. የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር፤
ለ. ወቅታቸዉን ያልጠበቁ የዝናብ ወራት መታየት፤
ሐ. ተደጋጋሚ የድርቅ መከሰት፤
መ. የወንዞችና ምንጮች የወኃ መጠን መቀነስ፤
ሰ. አደገኛና ደራሽ ጎርፎች በተደጋጋሚ መከሰት፤
ረ. በአግሮ ኢኮሎጂያዊ የአመራረት ዘይቤ ላይ የሚታዩ ለዉጦች መከሰት/መታየት፡፡

"በቆላና ወይና ደጋ አካባቢ በመብቀልና በማደግ የሚታወቁ ሰብሎችና እጽዋት በደጋ አካባቢዎች በቅለዉ ማደግ እና በደጋና ቀዝቃዛ አካባቢዎች በመብቀልና በማደግ የሚታወቁ ሰብሎችና እጽዋት ከአካባቢዎቹ መጥፋት ወይም የእነዚህ ዕጽዋትና ሰብሎች የምርት መጠን በዘላቂነት መቀነስ" የሚል መልስ የሰጠ ተሳታፊ በመልስ "ረ" ላይ የተመለከተዉን መልስ ብቻ በተዘዋዋሪ መንገድ እንደመለሰ ይቆጠራል፡፡

**የ1ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

ከአየር ንብረት ለዉጥ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ከተከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡ እነሱም፡- ተደጋጋሚ ጎርፍ እና ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተከስቷል/እየተከሰቱ ይገኛሉ ፤ የአከባቢ አየር ሙቀት ጨምሯል ፤ የመሬት ለምነት እና ምርታማነት ቀንሷል ፣ የአመራረት እና አኗኗር ዘይቤ ተለዉጧል ፣

ምንጮች እና ወንዞች እንዲሁም የሐይቆች የወኃ መጠን እጅግ ቀንሷል . . .!! እነዚህን መልሶች ከልዩ ልዩ ምሳሌዎች ጋር አዛምዶ ማቅረብም ትክክለኛ መልስ ሆኖ ይወሰዳል፡፡

**የ1ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 4ኛ ጥያቄ መልስ**

በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት በደጋማዉ የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ አግሮ ኢኮሎጂያዊ የአመራረት ሥርዓት ላይ ከተከሰቱ አዳዲስ ለውጦች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡ እነሱም፡-

1. በቆላማ አከባቢ ይመረቱ የነበሩት እንደ ጤፍ ፣ በቆሎ፣ ስኳር ድንች እና የመሳሰሉት ሰብሎች ወደ ደጋማዉ የወረዳዉ አከባቢ እየሸሹ/እየተመረቱ ነዉ ፤
2. ግራር እና ሌሎች አንዳንድ በቆላ አከባቢ ብቻ ይበቅሉ የነበሩ ዛፎች በደጋማዉ አከባቢ በቀላሉ መብቀል ጀምረዋል ፤
3. በደጋማዉ አከባቢ በሰፊ ይመረቱ የነበሩ እንደ አሞጭ/ቆልዖ/ ያሉ ሰብሎች በአሁኑ ሰዓት እየጠፉ ነዉ፡፡
4. በደጋማዉ አከባቢ ይመረቱ የነበሩ እንደ ገብስ ፣ ስንዴ ፣ አተር ፣ ባቄላ ፣ ድቡልቡል ድንች የመሣሠሉ ሰብሎች ምርታማነት ቀንሷል፡፡
5. ደጋማዉ አከባቢ ድሮ የነበረዉ የእርጥበት አዘል አየር በአሁኑ ሰዓት እየጠፋ እና በተራዉ ሞቃታማ እና የሚወብቅ አየር እየተስተዋለ ነዉ፤
6. በደጋማዉ አከባቢ ዝናብ እንደ ድሮዉ ወቅቱን ጠብቆ አይዘንብም፤ ይህም በምርታማነት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡

--------------------------------------//-------------------------------//----------------------------------------

## ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 2

ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**

**-----------------**

በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልክቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡

## የአየር ንብረት ለዉጥ ተግዳሮቶች በኢትዮጵያ

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-

አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኃላ፡-

1. የአየር ንብረት ለዉጥ በኢትዮጵያ እያስከተላቸው ያለዉን ተግዳሮቶች ይገነዘባሉ፤
2. ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ለአለም አየር ንብረት ለዉጥ በተለይ ለበካይ ጋዝ ልቀት ምን ያህል ድርሻ እያበረከተች እንደሆነ ይረዳሉ፡፡
3. ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዓለም በካይ ጋዝ ልቀት አሁን እየተጫወተች ያለችዉን ሚና በወቅቱ መቆጣጠር የማንችል ከሆነ በሀገሪቷ ሁለንተናዊ ልማትና የዜጎች ኑሮ ላይ ሊመጣ የሚችለውን አሉታዊ ሁኔታ ይገነዘባሉ፡፡
4. በ3 አስርተ አመታት ዉስጥ ብቻ በኢትዮጵያ ምን ያህል የተፈጥሮ አደጋዎች በተለይ በድርቅ መልክ እንደተከሰቱ ይገነዘባሉ፡፡
5. በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት በሚከሰቱ በሽታዎች ዙሪያ ግንዛቤ ያገኛሉ ፡፡

- ✓ በአሁኑ ወቅት ኢኮኖሚያቸዉ በአየር ንብረት በሚወሰን በተለይም በግብርና ላይ ጥገኛ በሆኑ ሀገሮች የአየር ንብረት ለዉጥ እያደረሰ ያለዉ ተጽዕኖ ለከፍተኛ <u>ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ</u> እየዳረጋቸው መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡

- ✓ የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ኢኮኖሚያቸው በከፍተኛ ሁኔታ የዝናብ ጥገኛ ሆኖ ዉሱን በሆነ የተፈጥሮ ሀብት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ለአየር ንብረት ለዉጥ ተጋላጭ ናቸው፡፡

- ✓ የግሎባል ልማት ማዕከል እ.ኤ.አ. በ2010 ያካኼደዉ ጥናት በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት ቀጥታ ተጋላጭነት ኢትዮጵያ ከ223 የዓለም ሀገራት 11ኛ ከፍተኛ ተጋላጭ ሀገር እንደሆነች ያመለክታል፡፡

- ✓ ይህ ተጋላጩነት የአየር ንብረት ለዉጥ የሚያመጣቸዉን አጠቃላይ ተጽእኖዎች ከመቋቋም አቅም ጋር ተነፃፅሮ ሲታይ ደግሞ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከዓለም 9ኛ ከፍተኛ ተጋላጭ ሆና ትገኛለች፡፡

- ✓ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት 2009 ዓ.ምን ጨምሮ ለብዙ አመታት በተደጋጋሚ ድርቅ የተጎዳ መሆኑ ለተጋላጭነታችን በቂ ማስረጃ ነው፡፡ .

- ✓ በሌላ በኩል በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ ለበካይ ጋዝ ልቀት የምታበረክተዉን አሉታዊ ሚና ስንመለከት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡

- ✓ በዘርፉ በተደረጉ ጥናቶች መሠረት ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፍ አየር ንብረት ለዉጥ የምታበረክተው ከ 0.03 ከመቶ በታች እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ሀገሪቱ ተጨማሪ የአየር ንብረት ለዉጥን የመከላከል ሥራዎች ካልሰራች እ.ኤ.አ. በ2030 በዓለም አቀፍ ደረጃ የበካይ ጋዝ ልቀት ድርሻዋ አሁን ላለው ከሃምሳ ፐርሰንት በላይ ይጨምራል፡፡

- ✓ ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሙቀት መጠን ለመግታት የተቀመጠዉን ግብ ማሳካት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው የሀገሪቱ የአየር ንብረት ለዉጥ ተቋቋሚ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ሰነድ ያመለክታል፡፡

- ✓ <u>**ድርቅ**</u> የምግብ እህል እጥረት በመፍጠር በኢትዮጵያዉያን ሕይወት ከፍተኛ ተጽእኖ እየፈጠረ እንዳለ እና በአሁኑ ወቅት ችግሩ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ እንዳልሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ህጻናት በምግብ እህል ዕጥረት ምክንያት የሚከሰቱ ማራስማስ፣ ክዋሽርኮርና የመተንፈሻ አካላትን ለሚያጠቁና ለሚጎዱ በሽታዎች ተጋላጭ ሆነዋል፡፡

- ✓ አይፒሲሲ የተሰኘ ተቋም ጥናት እንደሚያሳየው እ.ኤ.አ. ከ1983 - 2016 ባሉ 33 ዓመታት ዉስጥ ከስምንት ጊዜ በላይ በሀገሪቱ ድርቅ መከሰቱ ለዚህ በቂ ማሳያ ነዉ፡፡

- ✓ **<u>ጎርፍ</u>** ዜጎችን ለሞትና አካላዊ ጉዳት እንዲሁም ለወባ ፣ ኮሌራ/አጣዳፊ ተቅማጥ ፣ ታይፎይድ/ታይፈስና መሰል ተላላፊ በሽታዎች ከማጋለጡም በተጨማሪ ሐብትና ንብረታቸውን ለውድመት ይዳርጋል፡፡

- ✓ ኢትዮጵያን የመሰሉ ታዳጊ ሀገሮች በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት ለሚፈጠሩ በተለይም በጎርፎችና መሰል አደጋዎች ምክንያት ይሰቃያሉ፡፡

- ✓ ለምሣሌ በድሬዳዋ፤ በደቡብ ኦሞ በዳሰነችና ኛጋቶም እነደዚሁም በአካባቢያችን በአርባ ምንጭ ከተማ ኮንሶ ሰፈር ላይ፤ ልማት ሠፈር ላይ፤ በቀድሞው 02 እና 03 ቀበሌዎች እንደዚሁም ከአዲስ አበባ-አርባ ምንጭ- ጂንካ በሚወስደው ዋና መንገድ በኦቾሎ ላንቴ እና ዋጂፎ አካባቢ እንዲሁም በቆላ ሼሌ አካባቢ የደረሱ አውዳሚ ጎርፎች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

- ✓ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች ታዳጊ ሀገራት እነዚህን በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት በሚከሰቱ አደጋዎች የወደሙና የተጎዱ መሰረተ-ልማቶቻቸዉን ድጋሚ ለመገንባትና ለማገገም ደግሞ ተቋማዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፋይናንሳዊ አቅም የላቸዉም፡፡

- ✓ ጎርፍ በየትኛዉም ዓለም ይፈጠራል፡፡ ይሁን እንጂ የተጽእኖዉ ክባድነት በሀገራት የመቋቋም አቅም ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡ ለምሳሌ ያደጉ ሀገሮች ኢኮኖሚያዊ አቅማቸዉ ጠንካራ በመሆኑ ከፍተኛ የመቋቋም አቅም ያላቸዉ ሲሆን ኢትዮጵያን ጨምሮ በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ግን ኢኮኖሚያዊ አቅማቸዉ ገና እያደገ ያለ በመሆኑ የመቋቋም አቅማቸዉ እጅግ ደካማ በመሆኑ ለከፍተኛ ችግር ይጋለጣጋሉ፡፡

- ✓ የአየር ንብረት ለዉጥ ለ<u>**ግብርና ምርት መቀነስ**</u> ቀጥተኛ ድርሻ አለዉ፡፡ ማንኛዉም አካባቢያዊ የአየር ለዉጥ የእንስሳትና የእጽዋት ምርትን በቀጥታ ይጎዳል፡፡

- ✓ በመሆኑም በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት የሚከሰት ድርቅና ጎርፍ በተደጋጋሚ በተከሰቱ መጠን የግብርና ምርት መጠን ይቀንሳል፡፡

- ✓ ይህም ለምግብ እህል እጥረት እያጋለጠ የድሕነት ቅነሳ ጥረቶችን ውጤቶች ያኮስሳል::

- ✓ ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዘኛዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት ለሚከሰቱ አሳሳቢ የጤና ችግሮች የተጋለጡ ናቸዉ፡፡
- ✓ ለምሳሌ የምንተነፍሰዉ አየር ከተበከለ ፣ የምንጠቀመዉ ዉኃ እና ምግብ በአየር ንብረት ለውጥ ክስተቶች ምክንያት ጥራቱ ከተጎዳ ጤናማ መሆን አንችልም ማለት ነዉ፡፡
- ✓ ይህ የሚያመለክተን የአየር ንብረት ለዉጥ አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎችን በማናጋትና ለሰዉ ልጆች ምቾት በማሳጣት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀዉስ እንዲፈጠር ቀጥተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ነዉ፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. ከአየር ንብረት ለዉጥ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች ኢትዮጵያን እያጋጠሙ ካሉ ተግዳሮቶች መካከል 3ቱን ጥቀስ/ሽ፡፡
2. ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ለአለም አየር ንብረት ለዉጥ በተለይ ለበካይ ጋዝ ልቀት ምን ያህል ድርሻ እያበረከተች ትገኛለች?
3. አሁን ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዓለም በካይ ጋዝ ልቀት እየተጫወተች ያለችዉን ሚና በወቅቱ መቆጣጠር የማንችል ከሆነ እ.ኤ.አ. በ2030 የበካይ ጋዝ ልቀት መጠኗ በምን ያህል ፐርሰንት ሊጨምር ይችላል?
4. በ3 አስርተ አመታት ዉስጥ ብቻ በኢትዮጵያ ምን ያህል ድርቅ ተከስቷል?
5. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት ሊከሰቱ ከሚችሉ በሽታዎች 3ቱን ጥቀስ/ሽ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ2ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

ከአየር ንብረት ለዉጥ ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ምክንያቶች ኢትዮጵያን እያጋጠሙ ካሉ ተግዳሮቶች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡ እነሱም፡-

1. ተደጋጋሚ ድርቅ መከሰት ፤
2. ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብና ጎርፍ ተደጋጋሞ መከሰት ፤
3. የአከባቢ አየር ሙቀት መጨመር ፤
4. የግብርና ምርቶች መቀነስ ፣
5. ወባ ፣ ኮሌራ ሌሎችም ወኃ ወለድ እና አየር ወለድ በሽታዎች መከሰት ፡፡

እነዚህን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ምሣሌዎች ለአብነት የሚቀርቡ ከሆነ እንደ መልስ ሊወሰድ ይችላል፡፡

**የ2ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፍ አየር ንብረት ለዉጥ የምታበረክተው **ከ 0.03 ከመቶ በታች** እንደሆነ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

**የ2ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ተጨማሪ የአየር ንብረት ለዉጥን የመከላከል ሥራዎች ካልሰራች እ.ኤ.አ. በ2030 በዓለም አቀፍ ደረጃ የበካይ ጋዝ ልቀት ድርሻዋ አሁን ላለው **ከሃምሳ ፐርሰንት በላይ** ይጨምራል፡፡

**የ2ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 4ኛጥያቄ መልስ**

አይፒሲሲ የተሰኘ ተቋም ጥናት እንደሚያሳየው እ.ኤ.አ. ከ1983 - 2016 ባሉ 33 ዓመታት ዉስጥ **ከስምንት ጊዜ በላይ በሀገሪቱ ድርቅ** ተከስቷል፡፡

**የ2ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 5ኛ ጥያቄ መልስ**

ወባ ፣ ኮሌራ ፣ የምግብ እህል ዕጥረት ምክንያት የሚከሰቱ ማራስማስና ከዋሽርኮር ፣ የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቁና የሚጎዱ በሽታዎች ፣ ታይፎይድ/ታይፈስና መሰል በሽታዎች እና ሌሎች አየር ወለድ እና ዉሃ ወለድ በሽታዎች በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት ሊከሰቱ ከሚችሉ በሽታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

----------------------------------------------------------//----------------------------------------------------------------

## ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 3

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**

**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## የአየር ንብረት ለዉጥ መከሰት ዋና ዋና መንስኤዎች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. ለአየር ንብረት መከሰት ግንባር ቀደም መንስኤዎችን ይገነዘባሉ፤
2. የአየር ንብረት ለዉጥ መከሰት ተፈጥሯዊና ሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች መካከል የትኛዉ ከፍተኛዉን ድርሻ እንደሚይዝ ይገነዘባሉ፤
3. የሰዉ ልጆች በከባቢ አየር ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ካሳደሩባቸው ዘመናት አንጻር በተነጻጻሪነት በካይ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር በብዛትና በፍጥነት የተለቀቀው ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ ይረዳሉ፤
4. በታዳጊ ሀገሮች የሰዉ ልጆች ለአየር ንብረት ለዉጥ መከሰት ከሚጫወቷቸዉ ሚናዎች የትኛዉ የአንበሳዉን ድርሻ እንደሚይዝ ይገነዘባሉ፤
5. በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ዋነኛ መንስኤዎች ምን እንደሆኑ ይገነዘባሉ፡፡
6. በኢትዮጵያ የደኖች መመንጠርና የዛፎች መቆረጥ ለምን ዓላማ እንደሚተገበሩ ይረዳሉ፡፡

- ✓ ለአየር ንብረት ለዉጥ መከሰት ግንባር ቀደም መንስኤዎችን በሁለት ልንመድባቸዉ እንችላለን፡፡
- ✓ እነዚህ መንስኤዎች ተፈጥሯዊ እና ሰዉ ሰራሽ መንስኤዎች ናቸዉ፡፡
- ✓ በመሆኑም በዚህ ክፍል እነዚህ ሁለት መንስኤዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ዝግጅት እናቀርባለን፡፡

**የተፈጥሮ ኃይሎች** /Natural Forces/

- ✓ ከበረዶ ዘመናት እስከ ረጃጅም የሙቀት ዘመናት ድረስ ያሉ የሙቀት ሁኔታዎችን በማስተናገድ የምድራችን የአየር ሁኔታ ለብዙ ጊዜያት ተቀያይሯል፡፡
- ✓ በእነዚህ ክፍላተ ዘመናት እሳተ ገሞራንና ከፀሐይ የሚለቀቅ የሙቀት ኃይልን የመሣሠሉ የተፈጥሮ ኃይሎች ለምድር ሙቀት መጨመርና ለአየር ንብረት ለዉጥ የራሳቸዉን ሚና የተጫወቱ ቢሆንም በአንፃራዊ ሁኔታው ስንመለከት በነዚህ የተፈጥሮ ኃይላት የደረሰው ተጽዕኖ አናሳ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡
- ✓ ይህ የሚያሳየን የተፈጥሮ ኃይሎች በሰዉ ልጅ ጤና ፣ ኢኮኖሚ ፣ ህይወትና የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ የጎላ አለመሆኑን ነዉ፡፡

**ሰዉ ሰራሽ ድርጊቶች** /Human Activities/

- ✓ በሰዉ ልጅ ድርጊቶች ምክንያት የተቃጠለ በካይ ጋዝ በከባቢ አየር ውስጥ ያለውን ድርሻ እጅግ በሚያንር መጠን በፍጥነት መለቀቁ በግልጽ መታወቅ የጀመረዉ እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ነበር፡፡
- ✓ ዋነኛው የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ በከባቢ አየር ውስጥ የተቃጠለ አየርና የሌሎች በካይ ጋዞች ክምችት መብዛት ሲሆን ለዚህም አብይ ምክንያቶቹ የሰዎች ድርጊቶች በተለይም ከኢንዱስትሪና ከተሽከርካሪ ነዳጅ መቃጠል የሚወጣ ጭስ፣ የደን ምንጣሮና የደን ጭፍጨፋ የመሳሰሉ ተግባራት ናቸው፡፡

በጥናት የተረጋገጡ መረጃዎች የመሬት መራቆት (ለምነት መቀነስ) ከብዝሀ ሕይወት መመናመንና ከአየር ንብረት ለዉጥ ጋር የምክንያትና ዉጤት ትስስርሽ እንዳለው ያሳያሉ፡፡

- ✓ በተቃጠለ ጋዝ (ካርቦንዳይኦክሳይድ) ምክንያት የሚፈጠር የአየር ንብረት ለዉጥ እና የመሬት ለምነት መቀነስም እጅጉን የተቆራኙ እንደሆኑ እነዚህ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡
- ✓ ምክንያቱም የመሬት ለምነት መቀነስ እና የአየር ንብረት ለውጥ የተመጋጋቢነት ግንኙነት ስላላቸው፡፡

- ✓ የአየር ንብረት ለዉጥ በከባቢ አየር ላይ የሚከሰቱትን ወቅቱን ጠብቆ የሚመጣ ዝናብን ፣ የፀሐይ ጨረርን እና ንፋስን በማዛባት የመሬት መራቆትን (ለምነት መቀነስን) ሊያባብስ ይችላልና፡፡
- ✓ ይህ በእንዲህ እንዳለ በታዳጊ ሀገሮች በአጠቃላይ እና በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለይ የደን መመንጠርና መመናመን ዋነኛ የአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያቶች እንደሆኑ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡
- ✓ ሰዎች ደንን ለግንባታ ፣ ለማገዶ እንጨት ፣ ከተማን ለማስፋፋት፣ የእርሻ ሥራን ለማስፋፋት እና ለተመሣሣይ ዓላማዎች ይመነጥራሉ፡፡
- ✓ ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ በተጨባጭ እየተፈጠረ ያለ ሀቅ ሆኖ ቆይቷል፡፡
- ✓ አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳንም ብንመለከት በደን ሀብት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡
ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. ለአየር ንብረት መከሰት መንስኤ ከሚሆኑ ሁኔታዎች 2 ዋና ዋና የተፈጥሮ ሐይሎችን ጥቀስ/ሽ፡፡
2. ለአየር ንብረት ለዉጥ መከሰት ከተፈጥሯዊና ሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች መካከል የትኛዉ ከፍተኛዉን ድርሻ እንደሚይዝ ተናገረህ/ሽ ይህ እንዴት እንደሚረጋገጥ አብራራ/አብራሪ፡፡
3. የሰዉ ልጅ በከባቢ አየር ላይ የተቃጠለ ጋዝን ድርሻ እጅግ በሚያንር መጠንና ፍጥነት በመልቀቅ በአየር ንብረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ መታወቅ የጀመረው በየትኞቹ ዘመናት ነበር?
4. በታዳጊ ሀገሮች የሰዉ ልጆች ለአየር ንብረት ለዉጥ መከሰት በሚጫወቱት ሚና የትኞቹ መንስኤዎች ከፍተኛዉን ድርሻ ይይዛሉ?

5. በኢትዮጵያ ሰዎች ደንን ለምን እንደሚመነጥሩ እና ዛፎችን ለምን ዓላማ እንደሚቆርጡ አስረዳ/ጂ።

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ3ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

እሳተ ገሞራ እና ከፀሐይ የሚለቀቅ የሙቀት ሐይል ሁለቱ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሐይሎች ናቸው።

**የ3ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

ለአየር ንብረት ለዉጥ መከሰት ከተፈጥሯዊና ሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች መካከል ሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች ከፍተኛዉን ድርሻ ይይዛሉ።

ምክንያቱም ዋነኛው የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ በከባቢ አየር ውስጥ የተቃጠለ አየርና የሌሎች በካይ ጋዞች ክምችት መብዛት ሲሆን ለዚህም አብይ ምክንያቶቹ የሰዎች ድርጊቶች በተለይም ከኢንዱስትሪና ከተሽከርካሪ ነዳጅ መቃጠል የሚወጣ ጭስ፣ የደን ምንጣሮና የደን ጭፍጨፋ የመሳሰሉ ተግባራት ናቸው።

**የ3ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

በሰዉ ልጅ ድርጊቶች ምክንያት የተቃጠለ በካይ ጋዝ በከባቢ አየር ውስጥ ያለውን ድርሻ እጅግ በሚያንር መጠንና ፍጥነት መለቀቁ በግልጽ መታወቅ የጀመረዉ **እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ መጀመሪያ** አካባቢ ነዉ።

**የ3ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 4ኛ ጥያቄ መልስ**

በታዳጊ ሀገሮች በአጠቃላይ እና በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለይ **የደን መመንጠርና መመናመን ዋነኛ የአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያቶች እንደሆኑ ጥናቶች ያስረዳሉ።**

**የ3ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 5ኛ ጥያቄ መልስ**

በኢትዮጵያ ሰዎች ደንን **ለግንባታ ፣ ለማገዶ እንጨት ፣ ለከሰል፣ ከተማን ለማስፋፋት፣ የእርሻ ሥራን ለማስፋፋት እና ለተመሣሣይ ዓላማዎች ይመነጥራሉ።**

--------------------------------//-----------------------------//-----------------------------------------

## ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 4

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**


**አዘጋጆች**

**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**

**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**


**አቅራቢ**

**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## የአየር ንብረት ለዉጥ የዓለም አቀፍ አጀንዳ ስለመሆኑ የሚየሳዩ ታሪካዊ ዳራዎች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-

አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. ለአየር ንብረት ለዉጥ ቁልፍ ከሆኑ ስጋቶች ዉስጥ አንዱን ይገነዘባሉ፤
2. የደን መመንጠርና መመናመን ጉዳዮች ከመቼ ጅምሮ የዓለም መንግስታትና ህዝቦች አጀንዳ መሆን እንደጀመሩ ይረዳሉ፤
3. በታዳጊ ሀገሮች የሚፈፀሙ የደን መመንጠርና መመናመን ተግባራትን ለመቀነስ ፣ ለመከላከል እና ለመቀልበስ እንደ አስተማማኝ አማራጭ የቀረቡ የአየር ንብረት ለውጥ መከላከያ መፍትሄዎችን ይገነዘባሉ፤
4. በዓለም መንግስታት መካከል በሚደረጉ የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤዎች ላይ በሚተላለፉ ዉሳኔዎች መሰረት የአየር ንብረት ለዉጥን ለመከላከል በሚለቀቁ የገንዘብ ምንጮች እና በአስተዳደር ስርዓታቸው ዙሪያ ግንዛቤ ያገኛሉ፣

5. በኢትዮጵያ በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (በሬድ ፕላስ) ፕሮጀክቶች መካከል የሁምቦ እና ሶዶ ፕሮጀክቶችን ባህሪይ ፅንሰ-ሓሳባዊ ተሞክሮ ይቀስማሉ፡፡

- ✓ የአየር ንብረት ለዉጥ አሳሳቢ የሆነ የዓለም አከባቢያዊ እና ሰብአዊ ችግር ከሆነ ሰነባብቷል፡፡

- ✓ የዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለዉጥ ፓነል እ.ኤ.አ. በ2014 ያካኼደዉ ጥናት በምድር ወገብ አከባቢ የሚካኼድ የደን መመንጠርና የደን መመናመን ለአየር ንብረት ለዉጥ ቁልፍ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

- ✓ ይህ ጥናት የሚያሳየን እ.ኤ.አ. ከ2000 - 2009 ባሉ ዓመታት ብቻ በዚሁ በምድር ወገብ አካባቢ የተፈጸመ የደን መመንጠር እና የደን መመናመን ለአጠቃላይ የበካይ ጋዝ ልቀት 12 ፐርሰንት ድርሻ እንደነበረዉ ነዉ፡፡

- ✓ የደን መመንጠርንና መመናመንን መሰረት ያደረጉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ክርክሮች ካለፉ አስራ ሁለት ዓመታት ጀምሮ እጅግ ጨምረዋል፡፡
- ✓ ደኖች የአየር ንብረት ለዉጥን ለመቀነስ ካላቸዉ ፋይዳ የተነሳ የዓለም ሀገሮች እያካኼዱ ላሉት የአየር ንብረት ለዉጥ ድርድሮች ዋነኛ አጀንዳ አካል ናቸዉ፡፡
- ✓ የደን መመንጠርንና መመናመንን ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶች በካይ ጋዝን ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶች አካል ሆነው መወሰድ እንዳለባቸዉ የፖሊሲ አዉጪዎችና ተመራማሪዎች ይስማሙበታል፡፡

- ✓ በመሆኑም ካደጉ ሀገሮች በሚሰበሰብ የገንዘብ ድጋፍ በታዳጊ ሀገሮች የሚከሰትን የደን ሽፋን ክለትን ለመቀነስ ፣ ለመከላከልና ለመመለስ ሲባል ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራምን (REDD+) የመሳሰሉ አፋጣኝ የመፍትሄ አማራጮችን በመተግበር የደኖችን ወሳኝ ሚና ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን በዴንማርኳ ኮፐንሀገንና በሜክሲኮዋ ካንኩን ላይ የተደረጉት የአየር ንብረት ስምምነቶች አስምረውበታል፡፡

- ✓ የዓለም ባንክ ደግሞ አረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ በሚል ስም የተቋቋመዉን ተቋም በበላይነት እንዲመራና የገንዘብ ፍሰቱን እንዲያስተዳደር የተመረጠ ተቋም ነዉ፡፡

- ✓ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) የአየር ንብረት ለዉጥን ለመከላከል ወሳኝ ከሆኑ አሰራሮች አንዱ በመሆን ተመርጧል፡፡

- ✓ በመሆኑም የበለጸጉ ሀገራት ገበያ ተኮር የሆነ እና ግዴታን መሰረት ያደረጉ አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ የአየር ንብረት ለዉጥን ለመከላከል የሚደረገዉን የገንዘብ መዋጮ እንዲያዋጡ እና ከእነዚሁ ሁለት የገንዘብ መዋጮ አማራጮች አንዱን እንዲተገብሩ ወይም ሁለቱንም ጎን ለጎን እንዲያስኬዷቸዉ ምርጫ ተሰጥቷቸዋል፡፡

- ✓ ገበያ ተኮር የበካይ ጋዝ ንግድ ማለት አንድ በካይ ጋዝን የሚለቅ አገር ወይም ድርጅት አንድ በካይ ጋዝን በመከላከል ሥራ ላይ ከተሠማራ ወይም በደኑ ሐይል በካይ ጋዝን ከአየር በመምጠጥ ከሚያስወግድ አገር ወይም ድርጅት ጋር በመነጋገር በካይ ጋዝ ተከላካዩ ከአየር ላይ በሚያስወግደው የተሰላ የበካይ ጋዝ መጠን መሠረት ክፍያ የሚፈጽምበት አሠራር ነው፡፡

- ✓ ግዴታን መሠረት ያደረገው አሰራር ደግሞ አንድ በካይ ጋዝን የሚለቅ አገር ወይም ድርጅት የሚለቀውን በካይ ጋዝ ከአየር ላይ ለማስወገድ የሚያስችለውን የተሠላ የካርቦን ዋጋ እንዲከፍል ኮታ የሚጣልበት አሠራር ነው፡፡

- ✓ በዚህ ሁኔታ ገበያ ተኮር የበካይ ጋዝ ንግድ አማራጭ ዕቅድ ለሁለት አሠራሮች መመሥረት ምክንያት ሆኗል፡፡

- ✓ እነዚህም በዓለም ባንክ የደን ካርቦን አጋርነት ማስተባበሪያ እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሬድ ፈንድ በመባል የሚታቁት አሠራሮች ናቸው፡፡

- ✓ በሌላ በኩል ሁሉንም የአየር ንብረት ለዉጥ የካርቦን ገበያን መሰረት በማድረግና ከመንግስታት በሚሰበሰብ የግዴታ ገንዘብ አቅም ብቻ መከላከል/መቀነስ ከባድ በመሆኑ የግሉ ዘርፍ ከደን አልሚዎች ጋር በመደራደር የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክትበት አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን የዓለም መንግስታት አምነዉበታል፡፡

- ✓ በመሆኑም ገበያን ማዕከል ያላደረገዉ አማራጭ ከኢንዱስትሪዎቻቸዉ በካይ ጋዝን ከተፈቀደዉ ገደብ በላይ የሚለቁ ያደጉ ሀገሮች ካምፓኒዎች ደን በማልማት የበካይ ጋዝ ልቀትንና የአየር ንብረት ለዉጥን የመከላከል ተግባራት ከሚያከናዉኑ የአሳታፊ ደን ማህበራት እንዲገዙ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

- ✓ ለምሳሌ በደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በወላይታ ዞን ሁምቦ የሚገኘዉ የሬድ ፕሮጀክትና በሶዶ የሚገኘዉ የሬድ ፕሮጀክት እንደ ቅደም ተከተላቸዉ አስገዳጅ እና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የካርቦን ግብይት ፕሮጀክቶች ናቸዉ፡፡

- ✓ የሁምቦዉ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮጀክት እስከ አሁን በአፍሪካ ደረጃ ተግባራዊ ከተደረጉት የካርቦን ግብይት ፕሮጀክቶች በትልቅነቱ ቀዳሚ የሆነ አስገዳጅ የካርበን ግብይት ፕሮጀክት ነዉ፡፡

- ✓ በሌላ በኩል የሶዶው ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮጀክት ደግሞ አሳታፊ የደን ልማት ማህበራት ከካርቦን ገዥዎች ጋር ተደራድረው የካርቦን ግብይት ገቢ ተጠቃሚ እየሆኑበት ያለ የካርቦን ግብይት ፕሮጀክት ነዉ፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. በምድር ወገብ አካባቢ በተለይ በታዳጊ ሀገሮች ዉስጥ ከሚፈጸሙ ሠው ሠራሽ ተግባራት ለአየር ንብረት ለዉጥ ቁልፍ ከሆኑ ምክንያቶች ዉስጥ ዋንኛዉ ምንድነዉ?
2. የደን መመንጠርና መመናመን ጉዳዮች መቼ ነበር የዓለም መንግስታትና ህዝቦች ዋና አጀንዳ መሆን የጀመሩት?
3. በታዳጊ ሀገሮች የሚደረጉ የደን መመንጠርና መመናመን ተግባራትን ለመቀነስ ፣ ለመከላከል እና ለመቀልበስ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ አስተማማኝ አማራጭ የቀረበ የአየር ንብረት ለዉጥ መከላከያ መፍትሄ ምን ይባላል?
4. በዓለም መንግስታት መካከል በሚደረጉ የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤዎች በሚተላለፉ ዉሳኔዎች መሰረት የአየር ንብረት ለዉጥን ለመከላከል የሚለቀቁ የገንዘብ ምንጮችን እንዲያስተዳድርና ለታዳጊ ሀገሮች ለማስተላለፍ እንዲያመቻች ኃላፊነት የተሰጠዉ ተቋም ማን ነዉ?
5. በኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (የሬድ ፕላስ) ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በሁምቦ እና ሶዶ ፕሮጀክቶች መካከል ያለዉን አንድነትና ልዩነት አብራራ/ሪ።

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ4ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

የዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለዉጥ ፓነል እ.ኤ.አ. በ2014 ያካሄደዉ ጥናት **በምድር ወገብ አከባቢ የሚካሄድ የደን መመንጠርና የደን መመናመን ለአየር ንብረት ለዉጥ ቁልፍ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱና ዋነኛዉ እንደሆነ ያስረዳል።**

**የ4ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

የደን መመንጠርና መመናመን ጉዳዮች **ካለፉ አስራ ሁለት ዓመታት ጀምሮ** የዓለም መንግስታትና ህዝቦች ዋነኛ አጀንዳ ሆነዋል።

**የ4ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

**ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ይባላል።**

**የ4ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 4ኛ ጥያቄ መልስ**

በዓለም መንግስታት መካከል በሚደረጉ የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤዎች በሚተላለፉ ዉሳኔዎች መሰረት የአየር ንብረት ለዉጥን ለመከላከል የሚለቀቁ የገንዘብ ምንጮችን እንዲያስተዳድርና ታዳጊ ሀገሮች ለማስተላለፍ እንዲያመቻች ኃላፊነት የተሰጠዉ ተቋም **የዓለም ባንክ** ነዉ፡፡

**የ4ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 5ኛ ጥያቄ መልስ**

- ✓ በሁምቦ እና ሶዶ ፕሮጀክቶች መካከል ያለዉ **አንድነት** ሁለቱም ፕሮጀክቶች የበካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክቶች መሆናቸዉና በካርቦን ንግድ ዉስጥ ከገቡ የሀገሪቱ ፕሮጀክቶች መካከል መሆናቸዉ ነዉ፡፡

- ✓ በሁምቦ እና ሶዶ ፕሮጀክቶች መካከል ያለዉ **ልዩነት** የሁምቦ ፕሮጀክት አስገዳጅ የካርቦን ንግድ ፕሮጀክት ሲሆን የሶዶ ፕሮጀክት ግን በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የበካይ ጋዝ ቅነሳ ወይም ካርቦን ንግድ ፕሮጀክት ነዉ፡፡

--------------------------------//-----------------------------//-----------------------------------------

# ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 5

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልክቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## የደን መመንጠርና መመናመን መንስኤዎች እና ሬድ ፕላስ

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. ያደጉ ሀገሮች ኢንዱስትሪዎች ወደ ከባቢ አየር የሚለቁት በካይ ጋዝ ለዓለም አየር ንብረት ለዉጥ እያበረከተ ያለዉን ድርሻ ይረዳሉ፤

2. በኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለዉጥ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ያለዉ ምን እንደሆነ ይገነዘባሉ፤

3. አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳን ጨምሮ በስምንት ክልሎች ዉስጥ ባሉ በተመረጡ 26 የኢትዮጵያ ወረዳዎች የተደረገ ጥናት የለያቸውን የደን መመንጠርና መመናመን ዋና ዋና ምክንያቶች ይገነዘባሉ፤

4. የደኖች መመንጠርና መመናመን የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሚሆንበትን ምክንያት ይረዳሉ፡፡

- ✓ የአየር ንብረት ለዉጥ ሀገራችን ኢትዮጵያን በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳት ይገኛል፡፡

- ✓ በአለም ላይ ለሚከሰት የአየር ንብረት ለዉጥ በአጠቃላይ በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገሮች ፋብሪካዎች ወደ ከባቢ አየር የሚለቁት የበካይ ጋዞች ክምችት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡

- ✓ ታዳጊ ሀገሮች ለአለም የአየር ንብረት ለውጥ መከሰት የሚያበረከትቱት ድርሻ ከበለፀጉት አገሮች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ቢሆንም በታዳጊ ሀገሮችም ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሆኑ ተግባራት ይፈፀማሉ፡፡

- ✓ ኢትዮጵያን ጨምሮ በታዳጊ ሀገሮች ዋነኛ የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ ሆኖ የተመዘገበው የደኖች መመንጠርና መመናመን ነው፡፡

- ✓ ምክንያቱም በደኖች ውስጥ ሆነው የተቃጠለን አየር ከከባቢ አየር ላይ የሚስቡትና ለራሳቸው በምግብነት የሚጠቀሙት ዛፎች ተጨፍጭፈውና ተመንጥረው ሲነሱ ደኖች ስለሚመናመኑ የተቃጠለ አየር ክምችት በከባቢ አየር ላይ በዚያው ልክ ይጨምራል፡፡

- ✓ ሁለተኛ የተጨፈጨፈው ደን በልዩ ልዩ ምክንያት ሲነድም ሆነ መሬት ውስጥ ሲበሰብስ በዚሁ ሒደት የሚወጣው የተቃጠለ አየር እየተነነ የከባቢ አየርን የበካይ ጋዝ ክምችት ይጨምራል፡፡

- ✓ የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳን ጨምሮ በ26 የኢትዮጵያ ወረዳዎች በደን መመንጠርና መመናመን ዙሪያ የሀገራችንን ነባራዊ እዉነታ ያጠና አንድ ጥናት ለደን መመንጠርና መመናመን አባባሽ ሆነው እየቀጠሉ ያሉ ሰዉ ሰራሽ ተግባራትን እንደሚከተለዉ ለይቶ ያስቀምጣል፡፡

- **ነዳጅና የማገዶ እንጨት —**

- ✓ ከደንና ከእርሻ መሬት የሚሰበሰብ የማገዶ እንጨት የደን መመንጠርና መመናመን ዋነኛ ምክንያት ከሆኑ ሰዉ ሰራሽ ተግባራት አንደኛዉ ነዉ፡፡
- ✓ በተለይ እንደ አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ተጨባጭ ሁኔታ ከሰል ማክሰል እና ለቤት፣ ለሆቴሎች እንዲሁም ለሰው ኃይል አስተናጋጅ ተቋማት ፍጆታ የሚዉል የማገዶ እንጨት ለደን መመንጠርና መመናመን ዋነኛ ምክንያቶች ሆነው ተለይተዋል፡፡

- **የግንባታ እንጨት**

- ✓ አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ከፍተኛ የከተማ መስፋፋት ከሚታይባቸዉ የጋሞ ጎፋ ዞን ወረዳዎች አንዱ ነዉ፡፡
- ✓ ቤትን ጨምሮ ለአአንዳንድ የግንባታ ስራዎች ዛፎች በከፍተኛ ሁኔታ ይቆረጣሉ ፤
- ✓ በመሆኑም ይህም አንዱ የደን መመንጠርና መመናመን ምክንያት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

- **የአነስተኛ ማሳ ግብርናን ለማስፋፋት የሚደረጉ ተግባራት**

- ✓ የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በኢትዮጵያ በአታክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ስሙ-ጥር ከሆኑ አከባቢዎች በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች፡፡
- ✓ ዛሬ ላይ የምናየዉ በቆላማዉ የወረዳዋ አከባቢ ያለዉ በመስኖ የሚለማ መሬት ከጥቂት ዓመታት በፊት ሙሉ በሙሉ በደን የተሸፈነ ነበር፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ እነዚህ ዛሬ ላይ የምናያቸዉ የአታክልትና ፍራፍሬ ማሳዎች የተፈጠሩት ደን የነበረዉን መሬት በመመንጠርና ለእርሻ በማመቻቸት ነዉ፡፡
- ✓ ምንም እንኳን ለገቢ ማስገኛ እና በምግብ እህል ራስን ለመቻል አዎንታዊ ሚና የተጫወተ ቢሆንም ደን የነበረዉን ቦታ ለእርሻ ማሳ የማዋሉ ሂደት የደኖችን መመንጠርና መመናመንን አስከትሏል፡፡

- **ማሣን የማፈራረቅ እርሻ**

- ✓ ይህ የእርሻ አሰራር የሚከናወነዉ በተለይ በተዳፋታማዉ የወረዳዋ አከባቢ ባሉ ወይናደጋ እና ቆላ ቀበሌያት ነዉ፡፡
- ✓ በተዳፋታማ አካባቢዎች ደግሞ በደኖችና ጥሻዎች የተሸፈኑ ስፍራዎች በብዛት ይገኛሉ፡፡
- ✓ ከመሬቱ አቀማመጥ ጋር በተያያዘ አርሶ አደሮች በአንድ ቦታ እህል ደጋግሞ በመዝራት የተሻለ ምርት በተከታታይና በዘላቂነት ማግኘት የማይችሉ በመሆኑ የመሬቱ ምርታማነት በቀነሰ ቁጥር ያንን መሬት በማሳደር ደን የነበረዉን መሬት ለእርሻ የማዋል ልምድ አላቸው፡፡
- ✓ የተጠና የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ተግባራዊ ባለመደረጉ ምክንያት ይህ የአስተራረስ ሥርዓት የደን መመንጠርና መመናመን መንስኤ ሆኖ ቆይቷል፡፡

- **የሰደድ እሳት**

- ✓ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ክልል የሰደድ እሳት በመልቀቅ የተሻለ የግጦሽ ሳር አብቅሎ ለከብቶች መኖ መጠቀም የተለመደ ተግባር ነው፡፡
- ✓ እንዲሁም ለእርሻ ስራ ሲባል ተመንጥሮ በደረቀ የደን ቅጠላቅጥ ላይ እሳት መለኮስና ይህም በቸልተኝነት ሲተውት ወደ ደኖች ገብቶ ደንን የሚያቃጥልበትም ሁኔታም ይስተዋላል፡፡

- **የቤት እንስሳት እና ልቅ ግጦሽ—**

- ✓ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ የቤት እንስሳትን በመንጋ መልክ ወደ ደን ክልል በልቅ ማሰማራትና ሳር ማስጋጥ የቆየ ባህል ሆኖ እስከ ዛሬ ድረስ እየተከናወነ ነዉ፡፡
- ✓ ይህ ዓይነት የእንስሳት ልማት በእንስሳቱ ምርት ጥራት ላይ የራሱ የሆነ የጎንዮሽ ጉዳት ያለዉ ከመሆኑም በተጨማሪ ደንን እንስሳት እንዲረጋግጡና ዛፎችን እንዲገድሉ በማድረግም የራሱ አሉታዊ ድርሻ አለዉ፡፡

- **መጠነ-ሰፊ ዘመናዊ ወይም የመንግስት እርሻዎች መስፋፋት**

- ✓ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ክልል አሁን በዘመናዊ እርሻዎች የተያዘዉ የመሬት ክልል በሙሉ ክጥቂት ዓመታት በፊት በደን ተሸፈኖ እንደነበረ ግልጽ ነዉ፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 046881 - - - - በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. ለዓለም አየር ንብረት ለዉጥ ከፍተኛውን ድርሻ እያበረከተ ያለዉ ሠው ሰራሽ ተግባር ምንድን ነው?
2. በኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለዉጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው ሠው ሠራሽ ተግባር ምንድ ነው?
3. አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳን ጨምሮ በ26 የኢትዮጵያ ወረዳዎች የተደረገ ጥናት የለያቸውን የደን መመንጠርና መመናመን ዋና ዋና ምክንያቶች ዉስጥ ቢያንስ 3ቱን ዘርዝር/ሪ፤

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ5ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

በአለም ላይ ለሚከሰት የአየር ንብረት ለዉጥ በአጠቃላይ በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገሮች ፋብሪካዎች ወደ ከባቢ አየር የሚለቁት የበካይ ጋዞች ክምችት ከፍተናውን ድርሻ ይይዛል።

**የ5ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

በኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተዉ ሠዉ ሠራሽ ተግባር የደኖች መመንጠርና መመናመን ነው።

**የ5ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

የሚከተሉት አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳን ጨምሮ በ26 የኢትዮጵያ ወረዳዎች የተደረገ ጥናት የለያቸው የደን መመንጠርና መመናመን ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸዉ። እነሱም፡-

**ሀ.** ነዳጅና የማገዶ እንጨት፤
**ለ.** የግንባታ እንጨት፤
**ሐ.** የአነስተኛ ማሳ ግብርናን ለማስፋፋት የሚደረጉ ተግባራት፤
**መ.** ማሳን የማፈራረቅ እርሻ፤
**ሠ.** የሰደድ እሳት ፤
**ረ.** የቤት እንስሳት እና ልቅ ግጦሽ እና
**ሰ.** መጠነ-ሰፊ ዘመናዊ ወይም የመንግስት እርሻዎች መስፋፋት ናቸዉ።

------------------------------//---------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 6

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልክቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) እና የዓለም አቀፍ ጉዳይ የመሆኑ ጽንሰ ሀሳብ

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኂላ፡-

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ዓላማ ይገነዘባሉ፤
2. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ወደ ዓለም አቀፍ አጀንዳነት ስለደረሰበት ሒደት ግንዛቤ ያገኛሉ፤
3. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ከደን መመንጠርና መመናመን ጉዳይ ባሻገር ምን ምን ጉዳዮችን እንደሚያካትት ይረዳሉ፤

4. በዓለም አቀፍ ደረጃ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) የገንዘብ ፍሰትንና የቴክንክ ድጋፍን በተመለከተ በበላይነት የሚመሩ አካላትንና የሥራ ድርሻቸውን ይገነዘባሉ፤

5. ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አባል የሆነችዉ መቼ እንደሆነ እና ምን ምን ሥራዎችን እያከናወነች እንዳለች ይረዳሉ፤

- ✓ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ የደን ጭፍጨፋን ለማስቀም በሚል ዓላማ የተጠነሰሰ የአሠራር ሥልት ነዉ፡፡

- ✓ ይህ ሥልት ዓላማዉ የደን ጭፍጨፋን ከመከላከልና ከማስቆም ባለፈ ድህነትን ለመዋጋት እና ብዝሃ ሕይወትን በመጠበቅ የተስተካከለ ስነ-ምህዳራዊ ግልጋሎቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመፍጠርም የታሰበ ነዉ፡፡

- ✓ ብዙ ታዳጊ ሀገሮች አዲስና ራሱን የቻለ የደን ጭፍጨፋ መከላከያ መንገድ መቀየስ እንደሚያስፈልግ እ.አ.አ. በ2005 በካናዳ ሞንትሪያል በተካኸደዉ የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤ ላይ ይፋዊ ጥያቄ አቀረቡ፡፡

- ✓ በወቅቱ ያነሱት ጥያቄ በታዳጊ ሀገሮች ከደን መመንጠር የሚመጣን በካይ ጋዝ የመቀነስ አሰራር እንዲካተት የሚል ብቻ ነበር፡፡

- ✓ በኂላ ላይ በተደረገ ሰፊ ዉይይት ጉዳዩ ከደን መመንጠር ባሻገር

    - የደን መመናመንን፣
    - የጥብቅ ደኖች ሚናን ፣
    - ዘላቂ የደን ልማት ሥራን እና
    - የተቃጠለ አየርን በደን ዛፎች ዉስጥ የመያዝ ሥራዎችን የማጠናከር

ጉዳዮችን ጨምሮ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

- ✓ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ከላይ የተመለከቱ ሥራዎችን አካቶ ትርጉም የተሰጠዉ እና በቀጣይነት ባሉ የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤ ስምምነቶች ቦታ እንዲሰጠዉ ስምምነት የተደረሰበት እ.ኤ.አ. በ2007 በኢንዶነዥያ ሀገር ባሊ ከተማ በተካኼደዉ 13ኛዉ የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤ በተዘጋጀው የባሊ የድርጊት መርሀግብር በሚባለዉ ሰነድ ዉስጥ ነዉ፡፡

- ✓ ደኖች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚደረገዉ የአየር ንብረት ለዉጥ ቅነሳ ወሳኝ ሚና እንዳላቸዉ ታምኖበት የጋራ መግባባት ላይ የተደረሰዉ እ.ኤ.አ. በ2009 በዴንማርክ ሀገር ኮፐንሀገን ከተማ በተካኼደዉ 15ኛዉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤ ነዉ፡፡

- ✓ በሚቀጥለዉ ዓመት ማለትም እ.ኤ.አ. በ2010 በሜክሲኮ ሀገር ካንኩን ከተማ በተካኼደዉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤ ዝርዝር ጉዳዮችን ባካተተ መልኩ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አሠራር ላይ ዉሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡

- ✓ ያም ታዳጊ ሀገሮች ደንን መሰረት ባደረጉ ሥራዎች የአየር ንብረት ለዉጥ መከላከል ተግባራትን በማከናወን ለአየር ንብረት ለዉጥ ቅነሳ የበኩላቸዉን ድርሻ እንዲያበረክቱ የሚያበረታቱ ማዕቀፎችና ድጋፎች እንደሚያስፈልጉ ተመልክቷል፡፡

- ✓ ፕሮግራሙን ለመተግበር የሚያስችሉ የሀገራዊ ስትራቴጂዎችን የመቀየስ ፣ የደን መሰረታዊ መረጃ የመለየት ሥራዎችን ማከናወን ፣ የክትትል (ቁጥጥር) ሥርዓት መዘርጋት እና ማህበራዊ እና አካባቢያዊ የደህንነት ማእቀፎችን የማሟላት ሥራዎች በታዳጊ ሀገሮች እንዲከናወኑ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

- ✓ የበለፀጉ ሀገሮች ደግሞ ታዳጊ ሀገሮችን በዚህ ሥራቸው ዙሪያ በገበያ ተኮር እና ግዴታን መሠረት ባደረጉ የካርቦን ንግድ አሠራሮች አማካኝነት የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው እና የማበረታቻ ሥራዎችን እንዲከናዉኑ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

- ✓ ብዙ ሀገሮች የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤ ዉይይቶች የደን ዉድመትን የመቀነስ ፣ የመከላከልና ደኖችን ወደነበሩበት የመመለስ እና በካይ ጋዝን የመቀነስ ስራዎችን ከመስራት አኳያ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸዉን የጋራ ግቦች ለማሳካት የገንዘብ ድጋፍ ስርዓት በተሟላ መልኩ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ይናፍቃሉ፡፡

- ✓ ከዚህ አንፃር ሲታይ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) በሶስት ምዕራፎች እንዲፈጸም የዓለም ሀገራት ከስምምነት ደርሰዋል፡፡
- ✓ እነዚህ ምዕራፎች
    - የዝግጁነት ምዕራፍ ፣
    - የትግበራ ምዕራፍ እና
    - አፈጻጸምን መሰረት ያረደገና ተገቢዉ የደን ልማት ውጤት ልኬት ፣ የሪፖርት እና የማመሳከር ሥራ ከተሰራ በኂላ የሚፈጸም የክፍያ ምዕራፍ ተብለዉ ይጠራሉ፡፡
- ✓ በዚህ መሠረት አንድ በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት (REDD+) ውስጥ የተካተተ የደን አካል በዝርዝር በታቀደ የደን አጠቃቀም ሥርዓት ብቻ ጥቅም ላይ እየዋለ ከንክኪ፣ ከመመንጠርና መመናመን ነፃ ሆኖ ይጠበቃል፡፡
- ✓ በዚህም ሒደት ደኑ ለአየር ንብረት ለውጥ መከላከል ያስገኘው ፋይዳ ተሰልቶ፤ ሪፖርት ተደርጎና ተረጋግጦ የደኑ ጠባቂ ማህበረሰቦች በፕሮግራሙ በኩል የሚለቀቀው የገንዘብ ድጋፍ ተጠቃሚ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡
- ✓ ይሁን እንጂ የክፍያ ምንጮችና አፈጻጸማቸዉ አከራካሪ ሆነው የቆዩባቸው ጊዜያትም ነበሩ፡፡
- ✓ ምክንቱም አንዳንድ ሀገሮች የደን ካርቦንን ልክ እንደ ማንኛዉም ዕቃ ተገቢዉ ድርድር ተካሒዶበት በገዥና ሻጭ ፍላጎት የሚመራ የገበያ ስርዓት የሚደግፉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ አስገዳጅ የገንዘብ ድጋፍን በተመለከተ መልኩ መፈጸም አለበት የሚል አቋም ያራምዱ ነበረ፡፡
- ✓ እ.ኤ.አ. ከ2008 ጀምሮ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ባንክ በሚመራዉ በደን - ካርቦን አጋርነት ማስተባበሪያ አሠራር ውስጥ አባል በመሆን ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ዉስጥ እየተሳተፈች ትገኛለች፡፡
- ✓ በዚህም ሒደት ሀገራችን ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም ዝግጁነት ፣ ትግበራ እና ክፍያ አፈጻጸም ምዕራፎችን በባለቤትነት በማስተባበር የሀገሪቱን አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ራእይ ማሳካት የሚችል አደረጃጀት ዘርግታ እና ለዚህም ብሔራዊ ሴክሬተሪያት አቋቁማ ወደ ስራ ገብታለች፡፡

- ✓ የብሔራዊ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) በሚደግፍ የባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ስብስብ በሆነዉ የቴክንክ ድጋፍ ቡድን አስፈላጊዉ ሙያዊ ድጋፍ እየተደረገለት ይገኛል፡፡
- ✓ የፌደራል ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ስቲሪንግ ኮሚቴ ደግሞ በሀገር ደረጃ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ጠቅላይ ዉሳኔ ሰጪ አካል ሆኖ እየመራ ይገናል፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ማለት ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ/ጂ፡፡

2. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ፍፃሜ የሚያገኘው በስንት ምእራፎች ነው? ስማቸውን ጥቀስ/ሽ፡፡

3. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ዝርዝር ጉዳዮችን ባካተተ መልኩ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ለዉጥን ለመከላከል ተብሎ በይፋ የዓለም አጀንዳ የሆነዉ መቼ እና የት ሀገር በተካኸደው የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤ ነዉ?

4. ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዓለም ባንክ በሚመራዉ በደን - ካርቦን አጋርነት ማስተባበሪያ አባል የሆነችዉ መቼ እንደሆነ እና ምን ምን ሥራዎችን እያከናወነች እንዳለች በአጭሩ አስረዳ/ጂ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ6ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ የደን ጭፍጨፋን ለማስቆም ፣ የመሬት መራቆትን ለመቀነስ ፣ ደኖችን መልሶ ለማልማት፣ በተጠኑ ቦታዎች ችግኝ ተከላ በማከናወን አዳዲስ ደኖችን ለመፍጠር ፣ ገቢ ማዳበሪያ ስራዎች በመፍጠር ሰዎች ደኖች ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖ በመቀነስ የደንን ሀብት ለመጠበቅ እና የመሳሰሉ አሰራሮችን በመተግበር ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀዉን የበካይ ጋዝ መጠን ለመቀነስ የተዘረጋ የአሠራር ሥልት ነዉ፡፡

**የ6ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) በሶስት ምዕራፎች እንዲፈጸም የዓለም ሀገራት ከስምምነት ደርሰዋል፡፡

እነዚህ ምዕራፎች

- የዝግጁነት ምዕራፍ ፣
- የትግበራ ምዕራፍ እና

- አፈጻጸምን መሰረት ያረደገና ተገቢዉ የደን ልማት ውጤት ልኬት ፣ የሪፖርት እና የማመሳከር ሥራ ከተሰራ በኋላ የሚፈጸም የክፍያ ምዕራፍ ተብለዉ ይጠራሉ፡፡

**የ6ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) በዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ለዉጥን ለመከላከል ተብሎ ዝርዝር ጉዳዮችን ባካተተ መልኩ በይፋ የዓለም አጀንዳ የሆነዉ እ.ኤ.አ. **በ2010 በሜክሲኮ ሀገር ካንከን ከተማ በተካኼደዉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለዉጥ ጉባኤ ነዉ**፡፡

**የ6ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 4ኛ ጥያቄ መልስ**

እ.ኤ.አ. ከ2008 ጀምሮ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ባንክ በሚመራዉ በደን - ካርቦን አጋርነት ማስተባበሪያ አሠራር ውስጥ አባል በመሆን ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ዉስጥ እየተሳተፈች ትገኛለች፡፡

በዚህም ሒደት ፕሮግራሙን ማሳካት የሚችል ብሔራዊ ሴክሬተሪያት አቋቁማ እና ሌሎች አደረጃጀቶችን ዘርግታ ወደ ስራ ገብታለች፡፡

------------------------------//--------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 7

ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምአ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልክቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡

## ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አባል ሀገራት አንዷ የሆነችባቸዉ ምክንያቶች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. የሀገራችንን የአየር ንብረት ተቋቋሚ አረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ 4 ምሰሶዎች ይረዳሉ፤
2. የሀገራችን የደን ሀብት ምን ያህል ሄክታር እንደሆነና ብቻዉን ምን ያህል ቶን በካይ ጋዝን በውስጡ ይዞ በማስቀረት ለበካይ ጋዝ ቅነሳ ስንት መቶኛ ድርሻ እንደሚያበረክት ይገነዘባሉ፤
3. ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግሥታት ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) የዝግጁነት ምዕራፍ ዕቅዷን መቼ እንዳወጣች እና የፕሮግራሙ ፖሊሲ ቦርድ ታዛቢ የሆነችው ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ ግንዛቤ ያገኛሉ፤
4. በሀገራችን የደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) የዝግጁነት ምዕራፍ የመጀመሪያዉ ክልላዊ ሙከራ ፕሮጀክት የትኛዉ እንደሆነ ያውቃሉ፤

5. ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አባል ሀገር ሆና የተመረጠችበትን ምክንያት ይገነዘባሉ።

- ✓ ሀገራችን ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎችን መከላከል የሚያስችል የአየር ንብረት ለዉጥን ተቋቋሚ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂዋን እ.ኤ.አ. 2011 ነበር ሥራ ላይ ያዋለችዉ።
- ✓ ይህ ስትራቴጂ የአየር ንብረት ለዉጥን በመቋቋም ተጨማሪ የካርቦን ልቀት የማይከሰትበትን (zero net increase in carbon emissions) አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት እ.ኤ.አ. በ2025 መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ለመሆን ታልሞ የተወጠነ ሀገራዊ ስትራቴጂ ነዉ።
- ✓ ይህ ስትራቴጂ ከፍተኛ በካይ ጋዝ አመንጪ የሆኑ የእርሻ አሠራሮችን ወደ ዝቅተኛ አመንጪ አሰራሮች በማዞር ከመሬት አጠቃቀምና ከደን ዘርፍ አፈፃፀም ላይ የበካይ ጋዝ ልቀትን የመቀነስ ስልትን ይከተላል።
- ✓ በዚህም ሁኔታ ስትራቴጂው 4 ምሰሶዎችን መነሻ አድርጎ ይፈፀማል። እነሱም፡-

ሀ. የእርሻ አመራረት ልምዶችን ማሻሻል ፣

ለ. የደን ጥበቃ እና ልማት ተግባራትን ማከናወን ፣

ሐ. ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ማስፋፋት እና

መ. ዘመናዊና ኃይል ቆጣቢ አማራጮችን ወደ መጠቀም ልምዶች መሸጋገር ናቸው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በካይ ጋዝን ደን ዛፎች ዉስጥ ይዞ በማስቀረት የዓለም አየር ንብረት ለዉጥን ለመከላከል እምቅ አቅም እንዳላት ሀገሪቱ የነደፈችዉ የአየር ንብረት ለዉጥ ተቋቋሚ አረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ሰነድ ያመለክታል።

- ✓ አሁን በሀገሪቱ ያለዉ 12 ሚሊዮን ሄክታር ደን ከ2.7 ቢሊዮን ቶን በላይ በካይ ጋዝን በውስጡ አምቆ እንደያዘ ነዉ ይህ ሀገራዊ ሰነድ የሚያረጋግጠዉ።
- ✓ ይሁን እንጂ አሁን ያለዉን አዝማሚያ ስንመለከት በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ከሚከሰተው የበካይ ጋዝ ልቀት 1/3ኛው በደን መመንጠርና መመናመን ምክንያትነት የሚከሰት መሆኑ ተረጋግጧል።

- ✓ ሆኖም ወቅቱ ያመጣቸውን መልካም አጋጣሚዎች በአግባቡ መጠቀም ከቻልን አሁን ያለዉን የደን መመንጠርና መመናመን በመቀልበስ ደኖችን በድጋሚ በማልማት ኢኮኖሚያዊ እና ስነምህዳራዊ ጥቅሞችን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

- ✓ ለዚህም ተገቢ አሠራሮችን በመከተልና በካይ ጋዞችን በደን ዉስጥ አምቆ በማስቀረት ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ለመደገፍ ተብለዉ የሚለቀቁ የገንዘብ ድጋፎችን በመጠቀም ሀገራዊ ስትራቴጂዉን ስኬት መደገፍ ይቻላል፡፡

- ✓ ለአብነት ያህል በዚሁ አሠራር ውስጥ ገብተው በሀገራችን ተግባራዊ የተደረጉ ፕሮጀክቶችን ብንመለከት የባሌ ተራሮች ስነምህዳራዊ አካባቢ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያዉ ክልላዊ የዝግጁነት ምዕራፍ ሙከራ ፕሮጀክት ነዉ፡፡

- ✓ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ደግሞ የሀገሪቱን 60 በመቶ አግሮ ኢኮሎጂካል አካባቢ የሚወክል በመሆኑ በክልል ደረጃ ለዝግጁነት ምዕራፍ ሙከራ ፕሮጀክት የተመረጠ ክልል ነዉ፡፡

- ✓ በዚህ መሰረት በአሁኑ ሰዓት አካባቢያዊ እና ስነምህዳራዊ አቀማመጥን መሰረት ባደረገ አቀራረብ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እየተተገበረ ይገኛል፡፡

- ✓ በዚህም በክልል ደረጃ አሳታፊ የደን ልማትና አስተዳደር ማህበራት ተደራጅተዉ ይህ ፕሮጀክት በሚያስገኛቸው ውጤቶች በመታገዝ የተሻለ ጥቅም እያገኙ ይገኛሉ፡፡

- ✓ በነዚህ ፕሮጀክቶችና በሌሎች ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ሥራዎች ዙሪያ ግንዛቤ ለማሳደግና ሕዝባዊ ተሳትፎን ለማረጋገጥ ይረዳ ዘንድ የኦሮሚያ ክልልን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች በተመረጡና አማካይ በሆኑ ቦታዎች ላይ ሕዝብን ያሳተፉ የግንዛቤ ማዳበሪያና የምክክር ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

- ✓ እነዚህም ስራዎች የተሰሩት ሀገራችን ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም አባል ሆና መታቀፏን ተከትለው ነው፡፡

- ✓ ሀገራችን እ.ኤ.አ ከ2008 ጀምሮ የደን ካርቦን አጋርነት ማስተባበሪያ አባል ሆና ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ዉስጥ ስትሳተፍ የቆየች ቢሆንም በዚህ ፕሮግራም በአባልነት የታቀፈችው የራሷን አየር ንብረት ተቋቋሚ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ከነደፈች በኋላ ነዉ፡፡

✓ በመሆኑም ሀገራችን በዚህ ፕሮግራም የታቀፈችዉ ፕሮግራሙ ራሱ አገሪቱ ቀርፃ እየተገበረች ካለችው አየር ንብረት ተቋቋሚ አረንጓዴ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣም በመሆኑ ነዉ ፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. ከሀገራችን የአየር ንብረት ለዉጥ ተቋቋሚ አረንጓዴ የኢኮኖሚ ፖሊሲ 4 ምሰሶዎች ሁለቱን ጥቀስ/ሽ፡፡
2. የሀገራችን የደን ሀብት ምን ያህል ሄክታር እንደሆነ እና ብቻዉን ምን ያህል ቶን በካይ ጋዝን አምቆ ማስቀረት እንደሚችል ግለጽ/ጪ፡፡
3. ከኢትዮጵያ ክልሎች ከደን መመንጠርና መመናመን ለሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም የዝግጁነት ምዕራፍ የተመረጠዉ ክልል የትኛዉ እንደሆነ እና የተመረጠበትን ምክንያት አስረዳ/ጂ፡፡
4. ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አባል ሀገር ሆና የታቀፈችበትን ምክንያት አስረዳ/ጂ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ7ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

የሀገራችን አየር ንብረት ለዉጥ ተቋቋሚ አረንጓዴ የኢኮኖሚ ፖሊሲ 4 ምሰሶዎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

ሀ. የእርሻ አመራረት ልምዶችን ማሻሻል ፣

ለ. የደን ጥበቃ እና ልማት ተግባራትን ማከናወን ፣

ሐ. ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ማስፋፋት  እና

መ. ዘመናዊና ኃይል ቆጣቢ አማራጮችን ወደ መጠቀም ልምዶች መሸጋገር ናቸው፡፡

**የ7ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

አሁን በኢትዮጵያ ያለዉ 12 ሚሊዮን ሄክታር ደን ሲሆን ይህ ደን በዓመት ከ2.7 ቢሊዮን ቶን በላይ በካይ ጋዝን በውስጡ አምቆ እንደያዘ ነዉ የሀገሪቱ አየር ንብረት ለዉጥ ተቋቋሚ አረንጓዴ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሰነድ የሚያረጋግጠዉ፡፡

**የ7ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የሀገሪቱን 60 በመቶ አግሮ ኢኮሎጂካል አካባቢ የሚወክል በመሆኑ በክልል ደረጃ ለዝግጅት ምዕራፍ ሙከራ ፕሮጀክት የተመረጠ ክልል ነዉ፡፡

**የ7ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 4ኛ ጥያቄ መልስ**

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም አባል ሆና የታቀፈችዉ ፕሮግራሙ ራሱ አገሪቱ ቀርፃ እየተገበረች ካለችው አየር ንብረት ተቋቋሚ አረንጓዴ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣም በመሆኑ ነዉ፡፡

------------------------------//--------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 8

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ዋና ዋና ሰነዶች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኂላ፡-

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ዋና ዋና ሰነዶች ዙሪያ ግንዛቤ ያገኛሉ፤
2. በነዚህ ዋና ዋና ሰነዶች መሰረት በሀገሪቱ እየተሰሩ ያሉ ተግባራትን ይገነዘባሉ፤

✓ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ሥር እስከ አሁን አራት ዋና ዋና ሰነዶች ተዘጋጅተው የአሰራር መመሪያ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ እነሱም

- የማህበራዊ ፣ አካባቢያዊ እና ስትራቴጂካዊ ዳሰሳ ሰነድ ፤
- የማማከር እና ተሳትፎ ዕቅድ ሰነድ፤
- የሰፈራ ፖሊሲ ማዕቀፍ ሰነድ እና
- የቅሬታ አፈታት ሰነድ ዋና ዋዎቹ ናቸዉ፡፡

✓ እነዚህ ሁሉ ሰነዶች ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ማስፈፀሚያ መመሪያዎች ሆነው እየተተገበሩ ያሉ ናቸዉ፡፡

✓ የማህበራዊ ፣ አከባቢያዊ እና ስትራቴጂካዊ ዳሰሳ ሰነድ ( Social, Environmental & Strategic Assessment [SESA] Document) ዋና ዓላማዉ በፕሮጀክት አተገባበር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ማህበራዊ ፣ አከባቢያዊ እና ስትራቴጂክ ጉዳዮችን አስቀድሞ መለየትና የመፍትሄ እርምጃ ለመዉሰድ እንደ መመሪያ ሰነድ ሆኖ ማገልገል ነዉ፡፡

✓ ለምሳሌ በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት አተገባበር ሂደት የሴቶች ፣ ህጻናት ፣ አቅመ ደካሞች፣ አካል ጉዳተኞች ወይም በፕሮጀክቱ ምክንያት ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ሊደርስ የሚችል ችግርን አስቀድሞ በመለየት አደጋዉን የመቀነስ ወይም የማምከን እርምጃ ለመዉሰድ ይህ ሰነድ እንደ ሥራ መመሪያ ያገለግላል ማለት ነው፡፡

✓ በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ሥር የተዘጋጀው የማማከርና የተሳትፎ ዕቅድ ሰነድ (REDD+ Consultation & Participation Plan) ፕሮጀክቶች ከመተግበራቸዉ በፊትም ሆነ በትግበራ እንዲሁም በክትትል እና ግምገማ ወቅት ሁሉንም የማህበረሰብ እና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ዉይይት በማድረግ በሥራው ዙሪያ አስቀድሞ የማህበረሰብ እና ባለድርሻ አካላትን ሙሉ ይሁንታ ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር የተዘጋጀ የተሳትፎ ዕቅድ ሰነድ ነዉ፡፡

✓ በዚህ ሰነድ መሠረት በሚደረገው ውይይትና ምክክር ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ያለ ምንም ተጽእኖ ፣ ከትግበራ በፊት በሚደረጉ ዉይይቶችና ምክክሮች ያገኙትን መረጃ መሰረት በማድረግ ሙሉ ግንዛቤ ይዘው የፕሮጀክት ትግበራ ይሁንታቸውን ይሰጣሉ፡፡

✓ የሰፈራ ፖሊሲ ማዕቀፍ (Resettlement Policy Framework) በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት ምክንያት ቀደም ሲል ይኖሩ ከነበሩበት ሥፍራ የሚነሱ ከሆነ በምን ዓይነት መንገድ መስተናገድ እንዳለባቸዉ አቅጣጫ የሚያሳይ ጠቋሚ የፖሊሲ ሰነድ ነዉ፡፡

- ✓ በተለይ ይህ ሰነድ ምትክ መሬትን የመስጠት ፣ ካሳ የመክፈል እና ለተመሣሣይ ጉዳዮች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችሉ ድንጋጌዎች የተካተቱበት ሰነድ ነዉ፡፡
- ✓ የቅሬታ አፈታት ሰነድ (Grievance Redressing Guideline) ደግሞ በፕሮጀክት አተገባበር ሂዴት የሚፈጠሩ እና ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎች እና ያለመግባባቶች በምን ዓይነት አግባብ መፈታት እንዳለባቸዉ ዝርዝር አቅጣጫዎችን እና አካሄዶችን ያስቀምጣል፡፡
- ✓ ለምሳሌ ያለመግባባቶች በግለሰቦች መካከል ፣ በግለሰቦች እና በመንግስት ፣ በአሳታፊ ደን ልማት ማህበራት እና አባላቶቻቸዉ ፣ በአንዱ የአሳታፊ ደን ልማት ማህበር እና በሌላኛዉ መካከል ፣ በማህበረሰቦች እና ማህበረሰቦች መካከል ፣ በመንግስት ተቋማት መካከል ወይም በለጋሽ ድርጅቶች እና መንግስት መካከል ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡
- ✓ የቅሬታ አፈታት ሰነድ እነዚህ እና መሰል ችግሮች በምን ዓይነት አግባብ መፈታት እንዳለባቸዉ ግልጽ አቅጣጫ ፣ አሰራር እና አደረጃጀት ጭምር ያስቀመጠ ብሔራዊ ሰነድ ነዉ፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡
ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. የማማከርና ተሳትፎ ዕቅድ ሰነድን መሰረት በማድረግ የሚሠሩ ተግባራትን አብራርተህ አስረዳ/ጂ፡፡
2. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ሰነዶች መካከል በተለይ የቅሬታ አፈታት ሰነድ ከሚያተኩርባቸው ጉዳዮች አንፃር ቅሬታዎች ሊፈጠሩባቸው የሚችሉ አካላትን በጥንድ በጥንድ በማድረግ 2ቱን ተናገር/ሪ፡፡

3. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ሰነዶች ዉስጥ በተለይ ማህበራዊ ፣ አከባቢያዊ እና ስትራትጂካዊ ዳሰሳ ሰነድ ከሚያስገኛቸው ፋይዳዎች ቢያንስ 2ቱን ጥቀስ/ሽ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ8ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

የማማከርና የተሳትፎ ዕቅድ ሰነድን (REDD+ Consultaton & Participation Plan) በሠረት በማድረግ የሚፈፀሙ ተግባራት ፕሮጀክቶች ከመተግበራቸዉ በፊትም ሆነ በትግበራ እንዲሁም በክትትል እና ግምገማ ወቅት

1. ሁሉንም ማህበረሰብ እና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ዉይይት ማድረግና
2. በሥራው ዙሪያ አስቀድሞ የማህበረሰብ እና ባለድርሻ አካላትን ሙሉ ይሁንታ ማግኘት ናቸው፡፡

**የ8ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

ያለመግባባቶች በግለሰብ እና በግለሰብ መካከል ፣ በግለሰቦች እና በመንግስት ፣ በአሳታፊ ደን ልማት ማህበራት እና አባላቶቻቸዉ ፣ በአንዱ የአሳታፊ ደን ልማት ማህበር እና በሌላኛዉ መካከል ፣ በማህበረሰቦች እና ማህበረሰቦች መካከል ፣ በመንግስት ተቋማት መካከል፣ በለጋሽ ድርጅቶች እና መንግስት ወይም በካርቦን ገዢዎችና በማህበረሰቦች መካከል ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡

**የ8ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

የማህበራዊ ፣ አከባቢያዊ እና ስትራቴጂካዊ ዳሰሳ ሰነድ (Social, Environmental & Strategic Assessment [SESA] Document) ዋና ዓላማዉ በፕሮጀክት አተገባበር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ማህበራዊ ፣ አከባቢያዊ እና ስትራቴጂክ ጉዳዮችን አስቀድሞ መለየትና የመፍትሄ እርምጃ ለመዉሰድ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማግኘት ነው፡፡

ለምሳሌ በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት አተገባበር ሂደት የሴቶች ፣ ህጻናት ፣ አቅመ ደካሞች፣ አካል ጉዳተኞች ወይም በፕሮጀክቱ ምክንያት ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ሊደርስ የሚችል ችግርን አስቀድሞ በመለየት አደጋዉን የመቀነስ ወይም የማምከን እርምጃ ለመዉሰድ ይህ ሰነድ እንደ ሥራ መመሪያ ያገለግላል ማለት ነው፡፡

------------------------------//--------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ ስርጭት ክፍል 9

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) እና ዋና ዋና ሰነዶቹ በኢትዮጵያ የደረሱበት የአተገባበር ደረጃ

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን በባለቤትነት የሚያስተባብረውን ሀገራዊ ተቋም እና የተጠሪ ቢሮዎች፣ ኤጅንሲዎች ማስተባበሪያዎችና ጽ/ቤቶችን አደረጃጀት ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡

2. በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን በበላይነት ስለሚመሩ ብሔራዊ ኮሚቴዎችና ንኡሣን ኮሚቴዎች ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡

3. በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን አስመልክቶ በተሠሩ ክልላዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ዙሪያ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡

4. በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን አስመልክቶ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች በሚኖራቸው ሚና ላይ ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡

- ✓ ከዚህ በፊት ባቀረብናቸዉ ፕሮግራሞች ደጋግመን እንደገለጽነዉ ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ሀገሮች አንዷ መሆኗ ይታወቃል፡፡
- ✓ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሀገራችን በአሁኑ ሰዓት ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) የዝግጁነት ምዕራፍን እየተገበረች ትገኛለች፡፡
- ✓ የዚህ ምዕራፍ ሥራዎች በዋናነት
  - ፕሮገራሙን በበላይነት የሚያስተዳድር መዋቅራዊ አደረጃጀቶችን መመስረት ፣
  - የህግና ፖሊሲ ሰነዶችን ማዘጋጀት ፣
  - የሙከራ ፕሮገራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመተግበር እና ልምድ በመዉሰድ ለትግበራ ምዕራፍ የዝግጁነት ሥራዎችን ማከናወን
  - እንዲሁም በትግበራ ምዕራፍ ሊገጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስራዎችን መለየት
  - ለዚህም ይረዳ ዘንድ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ተገቢዉን መረጃ ማሰባሰብ እና የመተንተን ሥራዎችን መስራት
  - ከፕሮጀክቱ አካባቢ ማህበረሰብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ከጫና ነጻ የሆነ ምክክርና ዉይይት በማድረግ ይሁንታ ማግኘት ናቸዉ፡፡

- ✓ በዚህ መሰረት የአካባቢ፣ደን እና አየር ንብረት ሚኒስቴር በፌደራል ደረጃ ተመስርቷል፤
- ✓ በተጨማሪም በሀገር ደረጃ ፕሮግራሙን በባለቤትነት የሚያስተባብር ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ሴክሬተሪያት ተቋቁሞ ሥራውን እያከናወነ ይገኛል፤
- ✓ በክልል ደረጃ ከፌደራል መዋቅሩ ጋር በሚናበብ መልኩ ቢሮዎች ፤ ኤጀንሲዎችና ማስተባበሪያ አካላት ተዋቅረዋል፤

- ✓ ከክልል በታች ባሉ መዋቅሮች ደግሞ ሌሎች ማስተባበሪያ አካላትና ጽ/ቤቶች ተመስርተዋል ፤

- ✓ ለፕሮግራሙ አስፈላጊ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል ፤ የደን ህጎች ላይ ማሻሻያ ስራ ተሰርቷል።

- ✓ በፌደራል ደረጃ ፕሮግራሙን በበላይነት የሚመራ ብሔራዊ ስቲሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራውን እያከናወነ ይገኛል፤

- ✓ በፌደራልና ክልል ደረጃ ፕሮግራሙን በቴክኒካዊ ምክር ማገዝ የሚችሉ ኮሚቴዎች እና ግብረ-ኃይሎች ተመስርተዉ ወደ ስራ ገብተዋል።

- ✓ እነዚህን የዝግጁነት ምዕራፍ ስራዎች በመጠቀም ከዚህ በፊት በአጋር አካላት ሲተገበሩ የነበሩ ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችን ልምድ በመቀመርና አዲስ ብሔራዊ የሙከራ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ በተለይ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ፕሮግራሙ እየተሰራበት ይገኛል።

- ✓ እንደዚሁም ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ብሔራዊ ሰነዶች የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀይሰዉ ብዙ ተጨማሪ ስራዎች በሀገር ደረጃ ተሰርተዋል።

- ✓ ለምሳሌ ተከታታይ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ፕሮግራሞች ፣ ተዘጋጅተው የህዝብን ግንዛቤ የማሳደግ ስራዎች ትግበራ ቀጥሏል፤

- ✓ በሞባይል ስልክ የሚላኩ አጭር የጽሑፍ መልእክቶችን ጨምሮ በባርኔጣ ፣ ቲሸርት ፣ ባነር ፣ አጀንዳ ፣ ካለንደር እና በሌሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶች ስለፕሮግራሙ የህዝብን ግንዛቤ የማሳደግ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል።

- ✓ በተለይ በደ.ብ.ብ.ሕ.ክ ፣ በአማራ ፣ በትግረይ ፣ በጋምቤላ ፣ በቤንሻንጉል - ጉሙዝ እና በአፋር ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ፣ ባለሙያዎችን ፣ ተመራማሪዎችን ፣ የሴቶች እና የወጣቶች ተወካዮችን እንዲሁም የኃይማኖት አባቶችንና የሀገር ሽማግሌዎችን ያካተቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እና ዉይይቶች ተካሂደዋል።

- ✓ ዩኒቨርሲቲዎች በምርምር እና ስርጸት እንዲሁም በማህበረሰብ ልማት ይህንን ፕሮግራም እንዲያግዙ የሚያበረታቱ እንቅስቃሴዎች በሐዋሳ፣ በጅማና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች ተደርገዋል፤

- ✓ በየአከባቢዉ ባሉ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአከበቢ ጥበቃ ክበባት በየትምህርት ቤቱ ሚኒ ሚዲያ አማካኝነት ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ መልእክቶች የማስተላለፍ ዉጥኖች ታሳቢ ያደረገ ሀገር-አቀፍ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነዉ፤

- ✓ ዩኒቨርሲዎች እና ትምህርት ቤቶች ችግኝ ተከላ እና የደን እንክብካቤ ተግባራት በማከናወን የበኩላቸዉን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፤

- ✓ በዚህ ሂደት ውስጥ በአጠቃላይ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት የተሰጡ ሀሳቦች ፣ አስተያየቶች እና ትችቶች በሀገራዊ ሰነዶች ዉስጥ በግብአትነት ተካተዋል፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን በባለቤትነት የሚያስተባብረው ሀገራዊ ተቋም ምን ይባላል?

2. በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን አስመልክቶ በበላይነት የሚመራዉ ብሔራዊ ኮሚቴ ምን ይባላል?

3. በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን አስመልክቶ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ከሚኖራቸው ሚና 2ቱን ጥቀስ/ሽ።

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ9ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን በባለቤትነት የሚያስተባብረው ሀገራዊ ተቋም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የአከባቢ ፣ ደንና አየር ንብረት ለዉጥ ሚኒስቴር፣ ብሔራዊ የREDD+ ሴክሬታሪያት ይባላል።

**የ9ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን አስመልክቶ በበላይነት የሚመራዉ ብሔራዊ ኮሚቴ ብሔራዊ የREDD+ ስቲሪንግ ኮሚቴ ይባላል።

**የ9ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ጉዳይን አስመልክቶ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨረሲቲዎች ከሚኖራቸው ሚና የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ። እነሱም፡-

ሀ. በምርምርና ስርጸት ሥራዎች ችግር ፈቺ ሀሳቦችን ማፍለቅ፤

ለ. በምርምር የተገኙ ዉጤቶችን በመጠቀም የማህበረሰብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መስራት፤

ሐ. በማህበረሰብ ሬዲዮ ፣ ሚኒ ሚዲያ እና መሰል የማህበረሰብ ግንኙነት መሳሪያዎችን በመጠቀም ለማህበረሰብ ተደራሽ መሆን፤

መ. የአከባቢ ጥበቃ ክበባትን በማቋቋም የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤

ሠ. ማህበረሰቦቻቸዉን በማስተባበር ችግኝ ተከላና እንክብካቤ ማካሄድ እና መሰል ተግባራት ናቸዉ።

------------------------------//--------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 10

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምአ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልክቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

### የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) እና በዋና ዋና ሰነዶች አተገባበር ላይ የሰጠዉ ምላሽ

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኂላ፡-

1. የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ለደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አባል ሀገራት ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚሰጥ ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡

2. በአሁኑ ሰዓት የዓለም አቀፍ ግዴታዋን በመወጣት የኢትዮጵያን ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) በከፍተኛ ሁኔታ እየደገፈች ያለች ሀገር ማን እንደሆነች ያውቃሉ፡፡

3. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም ዙሪያ የዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ በሚያደርገዉ ድጋፍ ዙሪያ ጥሩ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

4. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አባል ሀገር መሆን የሚኖረውን የጥቅምና የሀላፊነት ፋይዳ ይረዳሉ፡፡

- ✓ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የኢትዮጵያን ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) በመደገፍ በኩል አዎንታዊ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡
- ✓ የድጋፉን ዓይነት በሁለት ከፍለን መመልከት እንችላለን፡፡
- ✓ አንደኛዉ የድጋፍ ዓነት የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን ሁለተኛዉ የድጋፍ ዓይነት ደግሞ ቴክኒካዊ ድጋፍ ነዉ፡፡
- ✓ በገንዘብ ድጋፍ በኩል ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አባል ሀገር ለመሆን ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ይፋዊ የአባልነት ጥያቄ አቅርባ ጥያቄዋ ተቀባይነት ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የማያቋርጥ የገንዘብ ድጋፍ እየተደረገላት ነዉ፡፡
- ✓ በዚህም ገንዘብ ለፕሮግራሙ መዋቅራዊ አደረጃጀት ከመመስረት እስከ ሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ ድረስ ዘርፈ ብዙ ስራዎች እየተሰሩ ናቸዉ፡፡
- ✓ የቴክኒካዊ ድጋፍን ስንመለከት ደግሞ ለሀገራችን ብዙ ዓይነት ቴክኒካዊ እገዛዎች እየተደረጉላት ነዉ ፡፡
- ✓ ለምሳሌ ከሌሎች የፕሮግራሙ አባል ሀገሮች ምርጥ ተሞክሮዎችን እንድትቀስም የሚያስፈልጉ ድጋፎችን ከማመቻቸት እስከ ሀገራዊ ሰነዶች አዘገጃጀት እና አተገባበር ላይ ባሉ ጉዳዮች የዓለም አቀፉ ህብተረሰብ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ እየሰራ ይገኛል፡፡
- ✓ ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ የራሷን ምርጥ ተሞክሮ ለሌሎች የፕሮግራሙ አባል ሀገሮች እድታካፍል በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በኩል እገዛ እየተደረገላት ይገኛል፡፡
- ✓ በአሁኑ ሰዓት በፕሮግራሙ ዙሪያ ለሀገራችን ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ እያደረጉ ያሉ ግንባር ቀደም የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አካላት የኖርዌይ መንግስት እና የዓለም ባንክ ናቸው፤
- ✓ በቀጠይነት ሀገሪቱን በዚህ ፕሮግራም አተገባበር ሂደት ለመደገፍ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ይፋዊ ይሁንታ ከመስጠት ባሻገር በተግባር ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በጋራ እየሰራ ይገኛል፡፡

- ✓ ሀገራችን ኢትዮጵ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አባል ስትሆን ፕሮግራሙ የሚፈጥራቸው ጥቅሞች ተጋሪ እና ፕሮግራሙ የሚያስከትላቸው ግዴታዎች ፈጻሚ ትሆናለች፡፡
- ✓ የፕሮግራሙን ትሩፋቶች ከመጠቀም በተጨማሪ ፕሮግራሙ የሚጠይቃቸውን ግዴታዎችን ከራሷ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ሙሉ በሙሉ ለማሟላት ፈርማለች ማለት ነዉ፡፡
- ✓ ይህ ደግሞ ሀገራችንን የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከማድረጉ በተጨማሪ እንደፈራሚነቷ ሁሉንም ግዴታዎች የመፈጸም ኃላፊነት ያሸክማታል ማለት ነዉ፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ለደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አባል ሀገራት ምን ዓይነት ድጋፎችን እንደሚሰጥ ግለጽ/ጭ፡፡
2. በአሁኑ ሰዓት የዓለም አቀፍ ግዴታዋን በመወጣት የኢትዮጵያን ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) በከፍተኛ ሁኔታ እየደገፈች ያለች ግንባር ቀደም ሀገር ማን ነች?
3. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አባል ሀገር መሆን ያለዉን የጥቅምና ሐላፊነት ፋይዳ አስረዳ/ጂ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ10ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ለደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አባል ሀገራት የገንዘብና የቴክኒካዊ ድጋፎችን ይሠጣል፡፡

**የ10ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

በአሁኑ ሰዓት የዓለም አቀፍ ግዴታዋን በመወጣት የኢትዮጵያን ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) በከፍተኛ ሁኔታ እየደገፈች ያለች ግንባር ቀደም ሀገር ኖርዌይ ትባላለች፡፡

**የ10ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አባል ሀገር መሆን ፕሮግራሙ የሚፈጥራቸው ጥቅሞች ተጋሪ እና ፕሮግራሙ የሚያስከትላቸው ግዴታዎች ፈጻሚ ያደርጋል፡፡ ጥቅሞቹ የገንዘብና ቴክኒካዊ ድጋፎች ሲሆኑ ግዴታዎቹ ደግሞ ከደን አስተዳደር ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ህጎችንና ፖሊሲዎችን ከማሻሻል አልፎ የሚሰጣቸዉን ቴክኒካዊ ድጋፍ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

------------------------------//--------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 11

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምአ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልክቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

### ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ትግበራ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አዎንታዊ ተጽእኖዎችን ለይተዉ ያዉቃሉ፤
2. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለይተዉ ያዉቃሉ፤
3. ከደን መመንጠርና መመናመን በሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽእኖዎች ማንን ሊጠቅሙና ሊጎዱ እንደሚችሉ ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡

- ✓ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ብዙ በጎ ተጽእኖዎች አሉ።
- ✓ እነዚህን በጎ ተጽእኖዎች ከተፈጥሮ አካባቢ ጠቀሜታ አንፃር ብንመለከት
  - የደን ብዝሃ ሕይወትን ይታደጋል፤
  - እየጠፉ ያሉ ዝርያዎች እንዲያገግሙ ያደርጋል፤
  - የደን መመናመንን በመቆጣጠር የደን ስነምህዳር የአየር ንብረት ለዉጥን እንዲከላከል ያስችላል።
  - አዳዲስ የደን ተከላ ሥራዎችንም ስለሚያበረታታ የደን ሽፋንን በማሳደግ ዘላቂ የደን ሐብት ተጠቃሚ ያደርጋል።
  - የደን ሽፋን በሚጨምርበት ወቅት ምንጮች ስለሚፈልቁ ለመጠጥ፣ ለቤት ውስጥ ፍጆታ፣ ለጽዳት፣ ለእርሻና ለግንባታ ሥራዎች በቂ የዉኃ አቅርቦት ይኖራል፤
  - በበቂ የደን ሽፋን ምክንያት ምንጮች በሚፈልቁበት ጊዜ የአካባቢው እጽዋትና እንስሳት እንደዚሁም የውኃ ውስጥ ፍጥረታት ንጹሕና አመቺ የውኃ አቅርቦት ያገኛሉ።
  - በዚህም ሒደት ተፈጥሮ ሚዛኗን ስለምትጠብቅ ምድሪቱ ከድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋዎች ትጠበቃለች።
- ✓ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ተፅዕኖዎች ከማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቻቸው አንፃር ብንመለከት
  - ደንን ሳይጎዱ ከሚሰሩ እንደ ንብ ማነብ፣ ሣር አሳድጎ ማጨድ፣ በደን ውስጥ የቅመማቅመም ዕፅዋትን ማምረት የመሣሠሉ የገቢ ማመንጫ ተግባራትን በማከናወን ገቢ ለማግኘት ያስችላል፤
  - ለበካይ ጋዝ ቅነሳ ሥራቸው ለማህበረሰቦች የሚከፈለው ገንዘብ በፍትሃዊ መንገድ ሲከፋፈል የማህበረሰብ አባላት የራሳቸዉን ሕይወት እንዲደጉሙ ያስችላቸዋል፤
  - ማህበረሰቦች ለበካይ ጋዝ ቅነሳ ሥራቸው የሚከፈላቸውን ገንዘብ የጋራ የሆኑ ሐብቶችን ለማፍራት ቢያውሉ ለማህበረሰቦች ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ከመፍጠርም አልፎ ለአባላት የሥራ ዕድል ሊፈጥር ይችላል። ለምሣሌ መኪና፣ ባጃጅ እና ሳይክል የመሣሠሉ ተሽከርካሪዎች ቢገዙ

ወይም የማህበረሰብ ወፍጮ ቢተከል በአንቀሳቃሽነት ወጣቶች ተቀጥረው እየሠሩ ለማህበረሰቡ ተጨማሪ ገቢ ሊያስገኙ ይችላሉ።

- አካባቢዉን ከሚጎበኙ የሀገር ዉስጥና የዉጪ ቱርስቶች ከሚገኝ ገንዘብ ማህበረሰቦች ተጨማሪ ገቢ ሊያገኙ ይችላሉ።

✓ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) በጉዳት መልክም ተፅዕኖዎችን ሊያስከትል ይችላል።

✓ እነዚህን ጉዳቶች ከተፈጥሮ አካባቢ አንፃር ስንመለከት

- በፕሮግራሙ በሚጠበቁ ደኖች ክልል አካባቢን የሚጎዱና በፍጥነት የሚወርሩ እጽዋት ሊፈጠሩ ይችላሉ፤
- በአዳዲስ ተከላዎች ምክንያት የተዳቀሉ የዛፍ ዝርያዎች አከባቢውን ሊወሩ ይችላሉ፤
- በደን መሸፈን የማይገባቸዉ የሳር ቦታዎች ያለ አግባብ በደን ሊሸፈኑ ይችላሉ።

✓ ጉዳቶቹን ከማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ጎናቸው ብንመለከት

- በግንዛቤ ጉድለት ወይም በአመለካከት ችግር ምክንያት መሬት አልባ በሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ከጥቅም ክፍፍል አንፃር የመገለል አደጋ ሊፈጠር ይችላል።
- ፕሮግራሙ በሚሸፍናቸው የደን ክልሎች ቀደም ሲል ባህላዊ ተግባራት በሚከናወኑባቸዉ እና የእምነት ስርዓቶች በሚፈጸሙባቸዉ ቦታዎች ላይ ሰዎች ባህላቸዉንና የእምነት ስርዓታቸዉን እንዳያካናዉኑ ሊያደርጋቸዉ ይችላል።
- ለበካይ ጋዝ ቅነሣ ስራቸው ለማህበረሰቦች የሚከፈለው ገንዘብ ለማህበረሰቡ ጥቅም ከመዋል ይልቅ በጥቂት ኃላፊዎች እጅ ወድቆ የሙስና እና ምዝበራ አደጋ ሊደርስበት ይችላል፤

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን። ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል። አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም። ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አዎንታዊ ተጽእኖዎች መካከል ሁለት የተፈጥሮ አካባቢ ተጽዕኖዎችን ጥቀስ/ሽ፡፡
2. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ ከሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎች መካከል ሁለት የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎችን ጥቀስ/ሽ፡፡
3. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አዎንታዊ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎች ማንን ሊጠቅሙ እንደሚችሉ አብራራ/ሪ፡፡
4. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ የተፈጥሮ አካባቢ ተጽእኖዎች ማንን ሊጎዱ እንደሚችሉ አብራራ/ሪ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ11ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አዎንታዊ ተጽእኖዎች መካከል የተፈጥሮ አካባቢ ተጽዕኖዎች ወይም ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡ እነሱም፡-

- የደን ብዝሃ ሕይወትን ይታደጋል፤
- እየጠፉ ያሉ ዝርያዎች እንዲያገግሙ ያደርጋል፤
- የደን መመናመንን በመቆጣጠር የደን ስነምህዳር የአየር ንብረት ለዉጥን እንዲከላከል ያስችላል፡፡
- አዳዲስ የደን ተከላ ሥራዎችንም ስለሚያበረታታ የደን ሽፋንን በማሳደግ ዘላቂ የደን ሐብት ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡
- የደን ሽፋን በሚጨምርበት ወቅት ምንጮች ስለሚፈልቁ ለመጠጥ፣ ለቤት ውስጥ ፍጆታ፣ ለጽዳት፣ ለእርሻና ለግንባታ ሥራዎች በቂ የዉኃ አቅርቦት ይኖራል፤
- በበቂ የደን ሽፋን ምክንያት ምንጮች በሚፈልቁበት ጊዜ የአካባቢው እጽዋትና እንስሳት እንደዚሁም የውኃ ውስጥ ፍጥረታት ንጹሕና አመቺ የውኃ አቅርቦት ያገኛሉ፡፡

- በዚህም ሒደት ተፈጥሮ ሚዛኗን ስለምትጠብቅ ምድራቱ ከድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋዎች ትጠበቃለች፡፡

**የ11ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡ እነሱም፡-

- በግንዛቤ ጉድለት ወይም በአመለካከት ችግር ምክንያት መሬት አልባ በሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ከጥቅም ክፍፍል አንፃር የመገለል አደጋ ሊፈጠር ይችላል፡፡

- ፕሮግራሙ በሚሸፍናቸው የደን ክልሎች ቀደም ሲል ባህላዊ ተግባራት በሚከናወኑባቸዉ እና የእምነት ስርዓቶች በሚፈጸሙባቸዉ ቦታዎች ላይ ሰዎች ባህላቸዉንና የእምነት ስርዓታቸዉን እንዳያካናዉኑ ሊያደርጋቸዉ ይችላል፡፡

- ለበካይ ጋዝ ቅነሣ ስራቸው ለማህበረሰቦች የሚከፈለው ገንዘብ ለማህበረሰቡ ጥቅም ከመዋል ይልቅ በጥቂት ኃላፊዎች እጅ ወድቆ የሙስና እና ምዝበራ አደጋ ሊደርስበት ይችላል፤

**የ11ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አዎንታዊ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎች

1. አሳታፊ የደን ልማት ማህበራትን ፣
2. የማህበረሰብ ቱሪዝም ማህበራትን ፣
3. ደንን በማይጎዱ የገቢ ማመንጫ ስራዎች የተሰማሩ ግለሰቦችን ይጠቅማሉ፡፡

**የ11ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 4ኛ ጥያቄ መልስ**

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ የተፈጥሮ አካባቢ ተጽእኖዎች

1. አሳታፊ የደን ልማት ማህበራትን ፣
2. የማህበረሰብ ቱሪዝም ማህበራትን ፣
3. ደንን በማይጎዱ የገቢ ማመንጫ ስራዎች የተሰማሩ ግለሰቦችን፣
4. ሴቶችን ፣ ህጻናትን ፣ አቅመ-ደካሞችንና ሁሉንም ማህበረሰቦች ሊጉዱ ይችላሉ፡፡

------------------------------//---------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 12

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ለሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሔዎች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኂላ፡-

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሄዎችን ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡
2. በአሉታዊ ተጽእኖዎቹ መፍትሄዎች አተገባበር ዙሪያ የህበረተሰቡን ሚና ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡
3. በአሉታዊ ተጽእኖዎቹ መፍትሄዎች አተገባበር ዙሪያ በመንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና ዙሪያ ጥሩ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

- ✓ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) እንደማንኛውም የልማት ፕሮግራም የራሱ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎች እንደሚኖሩት ከዚህ በፊት ባቀረብናቸዉ የሬድዮ ፕሮግራሞቻችን አይተናል፡፡
- ✓ በዛሬዉ ዝግጅታችን ደግሞ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎች እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉ እንመለከታለን፡፡

- ✓ የተቀናጀ የማህበረሰብ ልማት ስልቶችን በመከተል ለአሉታዊ ተፅዕኖዎች መፍትሔ ማበጀት ይቻላል፤ ለምሣሌ

  - ሥራ ፈላጊ የአካባቢ ወጣቶችን፣ መሬት አልባ የእደ-ጥበብ ባለሙያዎችን፣ ኑሮአቸው በደን ሐብቶች ላይ የተመሠረተ የማህበረሰብ አባላትን ለምሣሌ የማገዶ እንጨት ለቃሚዎችን እና የአካባቢውን ማህበረሰብ በሚያመቸው አኳኋን በማደራጀት ጠንካራ እና ዘላቂ የሆኑ አሳታፊ የደን ልማት ማህበራትን ማቋቋም ይቻላል፣
  - በዚህ ሁኔታ የተደራጁ ማህበራት የደን ጥበቃና ማልሚያ ክልል ተሰጥቷቸው ከንክኪ ነፃ በሆነ ሁኔታ ደኖቻቸውን እያለሙ የደን ሐብቶቹ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፤
  - በዚህ ዓይነቱ አሠራር የደን  ሐብቶች ጥቅም የሚገኘው
    - ➢ ማህበራቱ ለበካይ ጋዝ ቅነሳ ላበረከቱት አስተዋጽዖ ከሚሠጣቸው አለም አቀፍ ክፍያ፣
    - ➢ በደን ውስጥ የሚገኝን ደረቅ እንጨት ብቻ ሰብስቦ በመሸጥ ወይም በመጠቀም፣
    - ➢ የደን ዛፍን መጠቀም በሚያስፈልግበት ወቅት በዕድሜያቸው ምክንያት እንዲቆረጡ ማህበሩ የፈቀዳቸውን ብቻ በመጠቀም፣
    - ➢ የደን ልማቱ በሚፈጥረው የቱሪዝም መስሕብ ምክንያት አካባቢውን ከሚጎበኙ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች ከሚገኝ ገቢ፣
    - ➢ በማህበራቱ በሚለሙት ደኖች ውስጥ የቅመማቅመም እጽዋትን በማምረት፣
    - ➢ በደኖቹ ውስጥና በአካባቢው የንብ እርባታ ስራዎችን በማከናወን፣
    - ➢ በደኖቹ ውስጥ የእንስሳት መኖ ሣር በማሳደግ እንስሳትን አስሮ በመቀለብ፣

- ከደን ልማቱ ለማህበረሰቡ በጋራ በሚገኙ ገቢዎች ተሽከርካሪዎችን በመግዛትና ቀላል ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ለማህበረሰቡ ተጨማሪ ገቢ በማስገኘትና የስራ ዕድል በመፍጠር፣
- እንደዚሁም ማህበረሰቡ በሚያገኘው ገቢ ት/ቤትንና መንገድን የመሣሠሉ ተጨማሪ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ለአካባቢው በመሥራት ሲሆን ፕሮግራሙ ለሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች እነዚህን የመሣሠሉ መፍትሔዎች ማበጀት ይቻላል፡፡

- በሌላ በኩል ደግሞ ማህበራቱ የሚያለሟቸውን ደኖች በጥንቃቄ በማስተዳደር ወራሪ እጽዋትን በመቆጣጠርና በአዲስ ተከላ ወቅት ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑ የዛፍ ዝርያዎችን በመጠቀም ደኖቻቸውን ከወራሪና ከማይፈለጉ ድቅል ዛፎች ሊከላከሉ ይችላሉ፡፡
- አሁን በሀገራችን በስራ ላይ ያሉ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክቶች (REDD+) ይህንን አሰራር በመከተል አሉታዊ ተጽእኖዎችን የመቀነስ ተግባራትን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡
- በኦሮሚያ ክልል
  - በኦሮሚያ የደንና ዱር እንስሳት ጥበቃ ድርጅት እየተተገበሩ የሚገኙ ፣
- በወላይታ ዞን
  - በወርልድ ቪዥን እየተተገበሩ የሚገኙ የሁምቦ እና ሶዶ ፕሮጀክቶች ፣
- በባሌ ዞን
  - በፋርም አፍሪካ የተተገበሩ ፕሮጀክቶች
- እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ
  - በኢትዮ ዌትላንድስ እና ናቹራል ሪሶርስ ማነጅመንት አሶስየሽን እየተተገበሩ ያሉ ፕሮጀክቶች የሚከተሏቸዉ የመፍትሄ አማራጭ ሞደሎች በዋናነት ከላይ የተመለከትናቸዉ ናቸዉ፡፡
- እነዚህ ሞዴሎች ዘላቂ የደን ልማት ከማረጋገጥ በተጨማሪ በማህበረሰቡ ዘንድ የባለቤትነት ስሜት በማስረጽ በኩልም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፦ የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ

ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሄ ከሚሆኑ አሠራሮች ዉስጥ 2ቱን ጥቀስ/ሺ፡፡
2. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመቀነስ በሚሠራባቸው መፍትሄዎች አተገባበር ላይ የህበረተሰቡን ሚና በአጭሩ አብራራ/ሪ፡፡
3. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሄዎች አተገባበር ላይ የመንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና ምን መሆን አለበት ትላለህ/ያለሽ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ12ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

የሚከተሉት ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሄ የሚሆኑ ዋና ዋና አሠራሮች ናቸዉ፡፡

- ሥራ ፈላጊ የአካባቢ ወጣቶችን፣ መሬት አልባ የእደ-ጥበብ ባለሙያዎችን፣ ኑሮአቸው በደን ሐብቶች ላይ የተመሠረተ የማህበረሰብ አባላትን ለምሣሌ የማገዶ እንጨት ለቃሚዎችን እና የአካባቢውን ማህበረሰብ በሚያመቸው አኳኋን በማደራጀት ጠንካራ እና ዘላቂ የሆኑ አሳታፊ የደን ልማት ማህበራትን ማቋቋም ይቻላል፣
- በዚህ ሁኔታ የተደራጁ ማህበራት የደን ጥበቃና ማልሚያ ክልል ተሰጥቷቸው ከንክኪ ነፃ በሆነ ሁኔታ ደኖቻቸውን እያለሙ የደን ሐብቶቹ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፤
- በዚህ ዓይነቱ አሠራር የደን ሐብቶች ጥቅም የሚገኘው
    - ማህበራቱ ለበካይ ጋዝ ቅነሳ ላበረከቱት አስተዋጽያ ከሚሠጣቸው አለም አቀፍ ክፍያ፣

- በደን ውስጥ የሚገኝን ደረቅ እንጨት ብቻ ሰብስቦ በመሸጥ ወይም በመጠቀም፣
- የደን ዛፍን መጠቀም በሚያስፈልግበት ወቅት በዕድሜያቸው ምክንያት እንዲቆረጡ ማህበሩ የፈቀዳቸውን ብቻ በመጠቀም፣
- የደን ልማቱ በሚፈጥረው የቱሪዝም መስሕብ ምክንያት አካባቢውን ከሚጎበኙ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች ከሚገኝ ገቢ፣
- በማህበራቱ በሚለሙት ደኖች ውስጥ የቅመማቅመም እጽዋትን በማምረት፣
- በደኖቹ ውስጥና በአካባቢው የንብ እርባታ ስራዎችን በማከናወን፣
- በደኖቹ ውስጥ የእንስሳት መኖ ሣር በማሳደግ እንስሳትን አስሮ በመቀለብ፣
- ከደን ልማቱ ለማህበረሰቡ በጋራ በሚገኙ ገቢዎች ተሽከርካሪዎችን በመግዛትና ቀላል ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ለማህበረሰቡ ተጨማሪ ገቢ በማስገኘትና የስራ ዕድል በመፍጠር፣
- እንደዚሁም ማህበረሰቡ በሚያገኘው ገቢ ት/ቤትንና መንገድን የመሣሠሉ ተጨማሪ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ለአካባቢው በመሥራት ሲሆን ፕሮግራሙ ለሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች እነዚህን የመሣሠሉ መፍትሔዎች ማበጀት ይቻላል፡፡

**የ12ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመቀነስ በሚሠራባቸው መፍትሄዎች አተገባበር ላይ ህበረተሰቡ የሚከተሉ ሚናዎችን ሊጫወት ችላል፡፡

ሀ. በአሳታፊ የደን ልማት ማህበራት እና ግለሰቦች እንዲሁም በማህበረሰብ ተሳትፎ የሚለሙ ደኖችን በጥንቃቄ ማስተዳደር፤

ለ. ወራሪ እጽዋትን በመቆጣጠርና በአዲስ ተከላ ወቅት ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑ የዛፍ ዝርያዎችን በመጠቀም ደኖቻቸውን ከወራሪና ከማይፈለጉ ድቅል ዛፎች መከላከል፤

ሐ. በፕሮግራሙ ድጋፍ ከሚያገኙ ገቢዎች ት/ቤትንና መንገድን የመሣሠሉ ተጨማሪ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ለአካባቢው በመሥራት፤

መ. በአከባቢዉ ለሚገኙ ስራ ፈላጊ ወጣቶች መኪና ፣ ባጃጅ ፣ ቀላል እንዱስትሪዎች በማቋቋም የስራ ዕድል መፍጠርና የአከባቢዉ ልማት ማሳደግ እና ወዘተ . . .

**የ12ኛ ሳምንት የሬድዮ ፐሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሄዎች አተገባበር ላይ የመንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና እንደሚከተለዉ ነዉ፡፡

ሀ. መንግስት ህጎችን ፣ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማዉጣት ፣ በማስተባበር ፣ በመተግበርና በማስፈጸም የበኩሉን ሚና መጫወት አለበት፡፡

ለ. ባለድርሻ አካላት የመንግስትን ጥረት በበጀት ፣ በቴክኒክ እና በሞራል የመደገፍ ስራዎችን መስራት አለባቸዉ፡፡

ሐ. ባለድርሻ አካላት የመንግስትን ሕግ ፣ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መሰረት ባደረገ መልኩ መንሰቃቀስና ማህበረሰቡንና መንግስትን የማገዝ ሐላፊነት አለባቸዉ፡፡

------------------------------//---------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 13

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ ለሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎች መፍትሔዎችን በአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ እንደ ተሞክሮ የመዉሰድ አስፈላጊነት

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኂላ፡-

1. እስከ አሁን ባለዉ ሁኔታ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ የተከሰቱ የአየር ንብረት ለዉጥ ተጽእኖዎች ላይ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

2. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አዎንታዊ ተጽእኖዎችን በአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ እንደመልካም አጋጣሚ ለመጠቀም ስለሚረዱ አሠራሮች ግንዛቤ ያገኛሉ፤

3. በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ በሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎች ዙሪያ

መንግስት፣ ህብረተሰብና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ምን ሚና ሊኖራቸው እንደሚገባ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

- ✓ በአርባ ምንጭ እና በዙሪያዋ ያሉ ደኖች በአደጋ ላይ እንዳሉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡
- ✓ የእርሻ መሬትን ለማስፋፋት የሚደረግ ምንጣሮ ፣ ከሰል ለማምረት የሚደረግ የደን ዛፍ ጭፍጨፋ ፣ የማገዶ እንጨት ቆረጣ ፣ የቤትና የአጥር ግንባታ እንጨት ቆረጣ ፣ ልቅ ግጦሽ እና የደን ሰደድ እሳት እነዚህ ደኖች አደጋ ላይ እንዲወድቁ ካደረጉ ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡
- ✓ ከእነዚህ ምክንያቶች የተነሳ በአሁኑ ሰዓት የኩልፎ ወንዝንና ለአርባምንጭ ከተማ ስያሜ መነሻ የሆኑ እንዲሁም ለደኑ እና ለከተማዉ ሕዝብ ሕይወት የሆኑ አርባዎቹ ምንጮችን ጨምሮ ሌሎች ከደን ዉስጥ የሚፈልቁ ምንጮች የዉኃ መጠን በእጅጉ ቀንሷል፤
- ✓ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለአካባቢው መስህብ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የዓሣና አዞ ምርት መታወቂያ የሆኑት የጫሞ እና አባያ ሐይቆች መጠንም እየቀነሰ ይገኛል፡፡
- ✓ በተጨማሪም ከአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት መመናመን የተነሳ በአካባቢዉ ስነ-ምህዳርና የአየር ንብረት ላይ ለዉጥ በመከሰቱ ምክንያት ኑሯቸው ከደን ሐብቶች ጋር የሚያያዝ የማህበረሰብ ክፍሎችም ሆነ መላው ሕብረተሰብ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እየፈተፈጠረባቸው ይገኛል፡፡

- ✓ የከተማዉ ነዋሪዎችና በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ያሉ ለሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ የአታክልት እና ፍራፍሬ ምርት አቅራቢ የህብረተሰብ ክፍሎች በምርታቸው ፣ በከብቶቻቸዉ፣ በቤት ንብረቶቻቸው እና በቤተሰቦቻቸው ሕይወት ላይ ተደጋጋሚና አውዳሚ የጎርፍ አደጋዎች ደርሰዋል፡፡

- ✓ ጥቂት ምሣሌዎችን ብናነሣ በ1988 በላንቴና አካባቢው በደረሰ ከፍተኛ ጎርፍ የሙዝ፣ የማንጎ፣ የቲማቲምና የበቆሎ እርሻዎች የከፋ ጉዳት የደርሰባቸው ሲሆን የነዋሪዎች ቤቶችም በጎርፍ በመጥለቅለቃቸው ምክንያት በርካታ ሐብት ንብረት ወድሟል፤

- ✓ በ1990 በአርባ ምንጭ ከተማ በኮንሶ ሰፈር በተከሰተዉ ጎርፍ ምክንያት ከ30 በላይ የንፁሐን ዜጎች ህይወት ከማለፉም በተጨማሪ በርካቶች ቤት ንብረታቸውን አጥተውበታል፤

- ✓ በ2007 በተከሰተ ጎርፍ በአርባ ነምንጭ ከተማ በልማት አካባቢ 15 የሚሆኑ ቤቶች በጎርፍ በመጥለቅለቃቸው ነዋሪዎች የሐብትና ንብረት ውድመት ደርሶባቸዋል፤

- ✓ የዝናብ ወራትን ተከትሎ ለበርካታ ጊዜያት ከአዲስ አበባ ወደ አርባ ምንጭ እና ጂንካ በሚወስደዉ ዋና አስፋልት መንገድ ላይ የደረሱ ተደጋጋሚ የጎርፍ አደጋዎች መንገዱን በመዝጋት የትራንስፖርትና የንግድ ችግር አስከትለዋል፤ እንደዚሁም በከፍተኛ ወጪ የተገነቡ ድልድዮችን ጠራርገው በመውሰዳቸው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ኪሣራ ከማስከተላቸውም በላይ በዜጎች ዝውውር ዙሪያ ከፍተኛ እንግልትን ፈጥሯል።

- ✓ ይሁን እንጂ እነዚህንና የመሣሠሉትን ከአካባቢያዊ መመናመንና መራቆት የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቀልበስ እና ለመቀነስ በአካባቢው እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ደግሞ በቂ ያለመሆናቸዉ ሌላዉ አሳሳቢ ጉዳይ ነዉ።

- ✓ በሌላ በኩል የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ እና የሀገራችን መንግስት የአየር ንብረት ለዉጥን ለመቀነስ እየወሰዷቸዉ ያሉ እርምጃዎች ከላይ የተመለከትናቸውን ዓይነት በአርባ ምንጭ እና አካባቢዉ እየተከሰቱ ያሉትን አሉታዊ ተጽእኖዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቋቋም እና ለመቀነስ መልካም አጋጣሚዎች ሆነው እናገኛቸዋለን፤

- ✓ የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከደን መመንጠርና መመናመን በሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ከታቀፉት የሀገሪቱ ወረዳዎች አንዱ ነዉ።

- ✓ በመሆኑም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ለፕሮግራሙ ትግበራ ዝግጁ በማድረግ የሁሉንም አስተዋጽዖ በተገቢዉ መንገድ ስራ ላይ በማዋል ከላይ የተጠቀሱ ችግሮችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመፍታት ትክክለኛዉ ወቅት ላይ ነን ማለት ይቻላል፤

- ✓ ይህ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ዙሪያ የሚሠራው የግንዛቤ ማስጨበጫና አቅም ግንባታ ሥራ ከተከናወነ በኋላ በአርባ ምንጭ

ዙሪያ ወረዳ የሚገኙ የደን አካባቢዎች በፕሮግራሙ ታቅፈው የፕሮጀክት ፈፃሚ ቢሆኑ የአካባቢው ማህበረሰብ ቀደም ሲል ባቀረብናቸው ዝግጅቶች ያየናቸውን የፕሮግራሙን አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖዎች በመቆጣጠር ፕሮግራሙ የሚያመጣቸው ጥቅሞች ተካፋይ ይሆናል፤

- ✓ እንደዚሁም አካባቢው ከስነ-ምህዳር ቀውሶች አገግሞ የተፈጥሮ ሚዛኑ ወደተጠበቀለት አካባቢ በመቀየር ለሕዝቡ አመቺ የስራ፣ የምርትና የመኖሪያ አካባቢ ይሆናል፡፡

- ✓ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ አሁን በፕሮግራሙ ታቅፈው በስራ ላይ ካሉ ፕሮጀክቶች ተሞክሮዎችን መውሰድ ይቻላል፤
- ✓ ፕሮግራሙን ቀድመው በመጀመር እየተገበሩ ባሉ አካባቢዎች
  - በደን መመንጠርና መመናመን ምክንያት የተራቆቱ መሬቶችን በድጋሚ በደን መሸፈን ተችሏል፡፡
  - ሀገር በቀል ዛፎችም መልሰዉ አገግመዋል፤
  - የጠፉ የዱር እንስሳት ወደ ድሮ መኖሪያዎቻቸዉ እየተመለሱ ይገኛሉ፣
  - የደረቁ ምንጮች እየፈለቁ ይገኛሉ፤
  - ተፈጥሯዊ ስነምህዳር ራሱን በራሱ ወደ መጠበቁ እየሄደ ይገኛል፡፡
  - የአካባቢዉ ማህበረሰብ ደግሞ ከማህበረሰብ ቱሪዝም ፣ ከንብ ማነብ ፣ ከደን ልማት፣ ከእንስሳት ድለባ፣ ከወፍጮ ቤት፣ ከመስኖ ሥራ፣ ከተሽከርካሪ ባለቤትነት የስራ ዕድሎችና ገቢ ማመንጫ አማራጮች ቀርበዉለት የፕሮግራሙን ትሩፋቶች እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡
- ✓ በኢልካ ፈፃሚነት እየተተገበረ የሚገኘው ይህ ፕሮጀክትም ተመሣሣይ አሠራሮችን በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ በሙከራ ደረጃ በመትከል ማህበረሰቡ ተጠቃሚ ሚሆንበትን አሠራር ለመዘርጋት አቅዷል፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ

በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. እስከ አሁን ባለዉ ሁኔታ ከአካባቢ መመናመንና መራቆት ጋር ሊያያዙ የሚችሉ ሆነው በአርባ ምንጭ እና አከባቢዉ ከተከሰቱ አሉታዊ የተፈጥሮ ክስተቶች ዉስጥ 2 ጥቀስ/ሺ፡፡

2. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ትሩፋት ሆነው በአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ ሊተገበሩ ከሚችሉ ልምዶች 2 ጥቀስ/ሺ፡፡

3. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመከላከል የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ መንግስት እና ህብረተሰብ ምን ዓይነት ሚና መጫወት አለባቸው ትላለህ/ያለሽ?

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ13ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

እስከ አሁን ባለዉ ሁኔታ ከአካባቢ መመናመንና መራቆት ጋር ሊያያዙ የሚችሉ ሆነው በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ የተከሰቱ አሉታዊ የተፈጥሮ ክስተቶች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡ እነሱም፡-

ሀ. ለአርባምንጭ ከተማ ስያሜ መነሻ የሆኑ እንዲሁም ለደኑ እና ለከተማዉ ሕዝብ ሕይወት የሆኑ አርባዎቹ ምንጮችን ጨምሮ ሌሎች ከደን ዉስጥ የሚፈልቁ ምንጮች የዉኃ መጠን በእጅጉ ቀንሷል

ለ. የጫሞ እና አባያ ሐይቆችም በደለል እየተሞሉና መጠናቸው እየቀነሰ ይገኛል፡፡

ሐ. የከተማዉ ነዋሪዎችና በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ያሉ ለሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ የአታክልት እና ፍራፍሬ ምርት አቅራቢ የህብረተሰብ ክፍሎች በምርታቸው ፣ በከብቶቻቸዉ፣ በቤት ንብረቶቻቸው እና በቤተሰቦቻቸው ሕይወት ላይ ተደጋጋሚና አውዳሚ የጎርፍ አደጋዎች ደርሰዋል፡፡

መ. በ1990 በአርባ ምንጭ ከተማ በኮንሶ ሰፈር በተከሰተዉ ጎርፍ ምክንያት ከ30 በላይ የንፁሐን ዜጎች ህይወት ከማለፋም በተጨማሪ በርካቶች ቤት ንብረታቸውን አጥተውበታል፡፡

ሠ. በ2007 በተከሰተ ጎርፍ በአርባ ነምንጭ ከተማ በልማት አካባቢ 15 የሚሆኑ ቤቶች በጎርፍ በመጥለቅለቃቸው ነዋሪዎች የሐብትና ንብረት ውድመት ደርሶባቸዋል፡፡

ረ. የዝናብ ወራትን ተከትሎ ለበርካታ ጊዜያት ከአዲስ አበባ ወደ አርባ ምንጭ እና ጂንካ በሚወስደዉ ዋና አስፋልት መንገድ ላይ የደረሱ ተደጋጋሚ የጎርፍ አደጋዎች መንገዱን በመዝጋት የትራንስፖርትና የንግድ ችግር አስከትለዋል፤ እንደዚሁም በከፍተኛ ወጪ የተገነቡ ድልድዮችን ጠራርገው በመውሰዳቸው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ኪሣራ ከማስከተላቸውም በላይ በዜጎች ዝውውር ዙሪያ ከፍተኛ እንግልትን ፈጥረዋል፡፡

## የ13ኛ ሳምንት የሬድዮ ፐሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ

ከከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ትሩፋት ሆነው በአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ ሊተገበሩ ከሚችሉ ልምዶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡

ሀ. በደን መመንጠርና መመናመን ምክንያት የተራቆቱ መሬቶችን በድጋሚ በደን መሸፈን፤

ለ. ሀገር በቀል ዛፎችን መልሰዉ እንዲያገግሙ ማድረግ ፤

ሐ. አሳታፊ የደን ልማት ማህበራትን አቋቁሞ የአከባቢ ጥበቃ ስራዎችን ማከናወን፤

መ. ከደን መመንጠርና መመናመን ምክንያት የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ምክንያት የሚገኙ ክፊያዎች ለማህበረሰብ ገቢ ማዳበሪያና ለማህበረሰብ ልማት ማዋል፤

ሠ. የደረቁ ምንጮች እንዲፈልቁ የሚያስችሉ እንደ ችግኝ ተከላና ክብካቤ ፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና እንክብካቤ ፣ የተፋሰስ ስራዎችን መስራት ፣ ወዘተ. . . ናቸዉ፡፡

## የ13ኛ ሳምንት የሬድዮ ፐሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመከላከል የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ መንግስት እና ህብረተሰብ የሚከተሉትን ሚናዎችን መጫወት አለባቸው፡፡

ሀ. መንግስት በስራ ላይ ያሉ ከደንና አከባቢ ጥበቃ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን በአግባቡ መፈጸምና ማስፈጸም አለበት፡፡

ለ. መንግስት በሕግ እና ፓሊሲ አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ ክፍተቶችንና ድክመቶችን በወቅቱ ማረም እና የማስተካከያ እርምጃዎቸን መዉሰድ አለበት፡፡

ሐ. ሕዝብ ህጎችን ማክበር ፣ መተግበር ፣ ሕግ ጥሰዉ የሚገኙትን መምከር ፣ መጠቆም ፣ እና ከህግ አካላት ጋር ተባባሪ በመሆን በዘርፉ ፍትህ እንዲሰፍን ማድረግ አለበት፡፡

መ. የደን ልማት ማህበራት በመተታደሪያ ደንቦቻቸዉና በመንግስት ህግ መሰረት መንቀሳቀስና የበኩላቸዉን አወንታዊ ሚና መጫወት አለባቸዉ ፤ ግጭቶች በአባላት መካከል የሚፈጠሩ ከሆነ በደንቦቻቸዉና በመንግስት ህግ መሰረት መፍታት አለባቸዉ፡፡

------------------------------//--------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 14

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምአ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

### ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ዙሪያ ጥቅም የመጋራት አሰራሮች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት የሚፈጠሩ ጥቅሞችን ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡
2. በፕሮግራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ ከሚችሉ ጥቅሞች መካከል በተለይ በካይ ጋዝን በደን ዛፎች ዉስጥ ይዞ ማስቀረት ያለዉን ኢኮኖሚያዊ እና ስነምህዳራዊ ጥቅም ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡
3. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ማህበራዊ ጥቅሞችን በየፈርጃቸዉ ለይተዉ ጥቅሞቹ ለማህበረሰብ በሚኖራቸው ፋይዳ ላይ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

- ✓ በምድር ወገብ አካባቢ ያሉ ደኖችን ለመታደግ የሚደረጉ ማበረታቻዎች ከገንዘባዊ ጥቅም አልፈው አካባቢያዊ ስነምህዳርንና የብዝሀ ሕይወት ዝሪያዎችን ከመጠበቅ አንጻር ተጨማሪ ጥቅሞችን የሚያስገኙ እንደሆኑ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡
- ✓ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ሀገሮች ፣ ህዝቦች እና ማህበረሰቦች የደን ጭፍጨፋንና መመናመንን ለመቀነስ ለሚያደርጓቸዉ ጥረቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች የአካባቢያዊ እና ሀገራዊ ኢኮኖሚ ልማትን ለማሳደግ አቅም ያላቸዉ ማነሳሻዎች ናቸዉ፡፡
- ✓ ይህንን ፕሮግራም ለማበረታታት የሚደረጉ የገንዘብ ፍሰቶች በመላው ዓለም በዓመት ዉስጥ ብቻ እስከ 30 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ ሲሆን ይህ ከፍተኛ የገንዘብ ፍሰት ፕሮግራሙን ከድሃ - ተኮር ልማት ፣ ከብዝሀሕይወት ጥበቃ እና ከስነምህዳራዊ ደህንነት አንጻር ትርጉም ባለዉ መልኩ ማበረታታት የሚችል እንደሆነ ታምኖበታል፡፡
- ✓ ከዚህም ባሻገር ፕሮግራሙ ከሚያስገኛቸዉ ጥቅሞች መካከል ለማህበረሰብ አባላት በርካታ ጥቅሞችንና የጥቅም ክፍፍል መንገዶች ማየት እንችላለን፡፡ ለምሣሌ፡-
    - የማህበረሰብ ቱሪዝም ገቢዎችን በፍትሐዊነት ማስተዳደር፤
    - በማህበርም ሆነ በግል ንብ ማነብ ፣
    - ለበካይ ጋዝ ቅነሳ ሥራ የሚከፈሉ ገንዘቦችን በፍትሐዊነት መጠቀም፤
    - ደኖችን በፍትሐዊነት ለቅመማቅመም ምርት መጠቀም
    - በደኖች ውስጥ የእንስሳት መኖን በማምረት በፍትሐዊነት መጠቀም፣
    - በፕሮግራሙ ምክንያት በሚገኙ ገቢዎች ለማህበረሰቡ የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎችንና የመሠረተ ልማት ተቋማትን በፍትሐዊነት መጠቀም ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡
- ✓ አሁን በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት ስራ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በዚህ አሠራር የሚከተሉትን ጥቅሞች በተግባር ለማህበረሰቦች እና ለግለሰቦች በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ማረጋገጥ ችለዋል፡፡
- ✓ እነዚህም፡-

❖ በወላይታ ዞን ሁምቦ ወረዳ እና በባሌ ዞን ዉስጥ ትምህርት ቤቶችን ፣ ጤና ጣቢያዎችንና መሰል ማህበራዊ ተቋማትን ለማህበረሰቦች በመገንባት ጥራት ያለዉን የማህበራዊ አገልግሎት ተደራሽነት እንዲያድግ አስችለዋል፡፡

❖ በወላይታ ዞን ሁምቦ እና ሶዶ ዙሪያ ወረዳዎች እና በባሌ ዞን ከበካይ ጋዝ ቅነሣ ሥራ የሚገኝን ገንዘብ በመጠቀም ወፍጮ ቤት በመትከል የአከባቢዉ ማህበረሰብ አባላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርገዋል ፤

- ❖ በወላይታ ዞን በሁምቦ እና ሶዶ ዙሪያ ወረዳ እና በባሌ ዞን በግልና በማህበር የተገኘን ገንዘብ በመቆጠብ ጥሪት ማፍራት ከመቻላቸውም በላይ ለስራ አጥ የህብረተሰብ ክፍሎች የመኪና ኪራይና የቱሪዝም አስጎብኚ ድርጅቶችን በማቋቋም የተሻለ ኑሮን ፈጥረዋል ፤
- ❖ በበወላይታ ዞን ሁምቦ እና ሶዶ ዙሪያ ወረዳዎች እና በባሌ ዞን አሳታፊ የደን ልማት ማህበራት የተሰሩ የደን ልማት እና ተጓዳኝ ስራዎችን ለመጎብኘት ከሚመጡ ቱሪስቶችና የልምድ ልዉዉጥ ተሳታፊ አካላት የሚገኝ የኮቴ ክፍያን መጠቀም ችለዋል፤
- ❖ በፕሮግራሙ ምክንያት ከተከለለዉ ደን ዉስጥ የሚገኝ የሳር ሽያጭ ገቢ ተጠቃሚ ሆነዋል ፤
- ❖ በወላይታ ዞን ሁምቦ እና ሶዶ ዙሪያ ወረዳዎች እና በባሌ ዞን ደን ዉስጥና በመኖሪያ አካባቢያቸው የሚከናወን የንብ ማነብ ስራ ተጠቃሚ ሆነዋል ፤
- ❖ በባሌ ዞን በደን ዉስጥ ቅመማቅመምና ሌሎች ተክሎች በማልማት የተጨማሪ ገቢ ባለቤት ሆነዋል፤
- ❖ በወላይታ ዞን ሁምቦ ወረዳ ከበካይ ጋዝ ንግድ የተገኘን ገንዘብ በመጠቀም የእህል መጋዝኖችን በመገንባት በማከራየትና በርካሽ ጊዜያት እህሎችን ገስተዉ በመጋዝን በማከማቸት በዉድ ጊዜ አትርፈዉ በመሸጥ ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት ተችሏል፤

- ✓ ወደ ተግባር ሲገባ በማህበር የተደራጁ አሳታፊ የደን ልማት ማህበራት ከላይ የተመለከትናቸዉንና ሌሎች ገቢዎችን በዉስጠ ደንባቸው እና በሀገሪቱ ህጎች መሰረት ለማህበረሰብ አባላት በፍትሐዊነት ያዳርሳሉ ማለት ነው።

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን። ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል። አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም። ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል።

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ከሚፈጠሩ ጥቅሞች ቢያንስ 2ቱን ጥቀስ/ሺ።

2. ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ ከሚችሉ ጥቅሞች ዉስጥ በተለይ በካይ ጋዝን በደን ዛፎች ዉስጥ

ይዞ ማስቀረት የሚያስገኛቸውን ኢኮኖሚያዊ እና ስነምህዳራዊ ጥቅሞች በአጭሩ አብራራ/ሪ፡፡

3. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ ከሚችሉ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በተለይ ለቤተሰብ እና ለግለሰብ ሊገኙ የሚችሉ ቢያንስ 2 ጥቅሞችን ጥቀስ/ሽ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ14ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት የሚፈጠሩ ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ. በማህበርም ሆነ በግል ንብ በማነብ የተሻለ ገቢ ማግኘት፣

ለ. የማህበረሰብ ቱሪዝም ገቢዎችን በፍትሐዊነት በማስተዳደር ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት፤

ሐ. ደኖችን በፍትሐዊነት ለቅመማቅመም ምርት በመጠቀም ተጨማሪ ገቢ ማመንጨት፤

መ. በደኖች ውስጥ የእንስሳት መኖን በማምረት በፍትሐዊነት በመጠቀም የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣

ሠ. በፕሮግራሙ ምክንያት በሚገኙ ገቢዎች ለማህበረሰቡ የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎችንና የመሠረተ ልማት ተቋማትን በመገንባት የአከባቢዉ ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ፤

ረ. የተፈጥሮን አከባቢ በመጠበቅና በመንከባከብ የመስኖና የመጠጥ ዉኃ አቅርቦትን መጨመር

ሰ. የአየር ንብረት ለዉጥ አሉታዊ ተጽእኖዎችን በመከላከል የምግብ እህል ምርታማነት መጨመር ፤

ሸ. በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት ሊመጡ ከሚችሉ የጤና ጠንቆች ራስን ፣ ቤተሰብንና ማህበረሰብ በመጠበቅ ምርታማ የሰዉ ኃይል እንዲኖር ማስቻል፤

ቀ. የተስተካከለ የአከባቢ የሙቀት መጠን ማረጋገጥ ፤

በ. ወቅቱን የተበቀ የዝናብ እና የፀሐይ ወራትን ማግኘት መቻል፣ ወዘተ…፡፡

**የ14ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም በካይ ጋዝን በደን ዛፎች ዉስጥ ይዞ ማስቀረት የሚያስገኛቸው ኢኮኖሚያዊ እና ስነምህዳራዊ ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ. በአለም የካርቦን ገበያ በመሳተፍ የበካይ ጋዝ ቅነሳ ስሌት ክፍያዎች ማግኘት፤

ለ. አካባቢያዊ ስነምህዳርንና የብዝሀ ሕይወት ዝሪያዎችን መጠበቅ፤

ሐ. የአየር ንብረት ለዉጥን መከላከል፡፡

**የ14ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ ከሚችሉ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በተለይ ለቤተሰብ እና ለግለሰብ ሊገኙ የሚችሉ ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ. ገቢ ማስገኛ ስራዎችን በመስራት ለግል እና ለቤተሰብ ጥሪት ማፍራት፤

ለ. በፕሮግራሙ ምክንያት የሚገነቡ እንደ ትምህርት ቤት እና ጤና ጣቢያ ያሉ ማህበራዊ ተቋማትን በቅርበት በማግኘት ጥራት ያለዉን አገልግሎት ማግኘት፤

ሐ. በፕሮግራሙ ድጋፍ መንገድ እና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን ማግኘት፤

መ. በፕሮግራሙ ድጋፍ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን በመጠቀም የተሻለ ሕይወት መምራት፤ ወዘተ . . .፡፡

-------------------------------//---------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 15

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ በሚችሉ ቅሬታዎችና ዓለም አቀፍ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ዙሪያ ግንዛቤ ያገኛሉ፤

2. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በአለም አቀፍ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ መከተል ስለሚገባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

3. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን ወጪ ቆጣቢ እና ልማትን በማይጎዳ መልኩ መፍታት የሚኖረውን ፋይዳ ይገነዘባሉ፤

4. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን ከማስተናገድ እና ከመፍታት አንጻር ለጋሾች፣ የካርቦን ገዥዎች እና የፕሮግራሙ ተግባሪ መንግስታት ምን ዓይነት ሚና መጫወት እንደሚገባቸዉ ግንዛቤ ኖራቸዋል፡፡

## በዓለም አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የግጭት አፈታት ስርዓቶች

- ✓ ዓለም አቀፋዊ የቅሬታ አፈታት አሰራሮች ግልጽ አሰራሮችን በመከተል ከፕሮግራሙ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ቅር ተሰኝተናል የሚሉ ቡድኖች ወይም ባለድርሻ አካላት ወይም መንግስት ቅሬታቸዉ የሚፈቱባቸዉ አሰራሮች ናቸዉ፡፡

- ✓ እነዚህ አሰራሮች በዋናነት ቅሬታዎችን በመቀበል ፣ በመመዝገብ ፣ በመመርመር እና እንደየባህሪያቸዉ በመፍታት ይከናወናሉ፡፡

- ✓ በነዚህ አሠራሮች ቅሬታዉ ከተፈጠረበት ማህበረሰብ አካባቢ እስከ ዓለም አቀፍ የቅሬታ ፈቺ አካላት ድረስ ያለውን የቅሬታ አፈታት ስርዓት በመከተል ይፈታል፡፡

- ✓ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ጋር የተያያዙ የቅሬታ አፈታት መንገዶች አሁን በስራ ላይ ያሉ የዳኝነትና የፍርድ ሥርዓቶችን ሊጠቀሙ አይችሉም ማለት አይደለም፡፡

- ✓ ይልቁን ቅሬታዎች በእነዚህ አሰራሮች መፈታት ካልቻሉ ለተጎጂዎች አማራጮችን ለማስፋትና ተጎጂዎች አስተማማኝ የህግ ጥበቃ እንዲያገኙ ለማድረግ ሲባል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚነት ያላቸው የቅሬታ አፈታት ስርዓቶች ለመስተንግዶ ክፍት ናቸው፡፡
- ✓ የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ በመቀነስ አረንጓዴ የኢኮኖሚ ልማትን ማረጋገጥ ቢሆንም ሁሉም ባለድርሻ አካላት በሥራውና በጥቅም ዙሪያ የየራሳቸዉ ፍላጎቶች ይኖሯቸዋል፤

- ✓ ከፍላጎቶቻቸው መለያየት የተነሳ ጥቅማችን ተነክቷል ብለው ሲያስቡ የየራሳቸዉን ጥቅም ለማስጠበቅ ቅሬታ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡

- ✓ የጥቅም ክፍፍል ፣ የደን ሀብትን በነጻነት የመጠቀም ፣ የመሬት ወይም የደን ይዞታ ማረጋገጫ ጉዳይ ፣ ከካርቦን ግብይት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ፣ ደኖችን ከማስተዳደር ወይም ከበጀት አመዳደብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ የሙስና ጉዳይ ወይም በዉል መሰረት ያለመክፈል ጉዳዮች ዋና ዋና የቅሬታ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

- ✓ የቅሬታ መንስኤዎቹ ምንም ይሁኑ ምንም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ አማራጭ የቅሬታ መፍቻ መንገዶችን ስንመለከት ዉይይት (negotiation) ፣ ድርድር (mediation) እና ግልግል ዳኝነት (arbitration) ዋና ዋና የቅሬታ አፈታት ዘዴዎች ናቸዉ፡፡
- ✓ በዉይይት ቅሬታዎች በሚፈቱበት ጊዜ ያለ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ሁለቱ ወገኖች እርስ በርስ በጠረጴዛ ዙሪያ በመወያየት ነዉ ቅሬታቸዉን የሚፈቱት፡፡
- ✓ ቅሬታዉ በድርድር የሚፈታዉ ደግሞ በሶስተኛ ወገን ወይም በአደራዳሪ ሽማግሌ አማካኝነት ነዉ፡፡
- ✓ በድርድር ውስጥ አደራዳሪ ሽማግሌዉ ሁለቱን ቅር የተሰኙ ወገኖች ለማግባባት ከመምከር ያለፈ ምንም ዓይነት ገዥ እና አስገዳጅነት ያለዉን ተፈጻሚ ዉሳኔ የመስጠት ስልጣን አይኖረውም፡፡
- ✓ ቅሬታዎች በሀገር ዉስጥ በሚደረግ ግልግል ዳኝነት የሚፈቱ ከሆነ ከወጪም ሆነ በቀጣይነት በግለሰቦች መካከል ሊኖር በሚችለዉ ግንኙነት መልካም ዉጤት ይኖራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ምክንያቱም የግልግል ዳኝነት አስገዳጅ ዉሳኔዎችን ከማሳለፍ ባለፈ ሁለቱም ወገኖች አስማምቶ እና እኩል አሸናፊ አድርጎ ነዉ ለጉዳዩ መቋጫ የሚያበጀዉ፡፡
- ✓ በሌላ በኩል ጉዳዮች ወይም ቅሬታዎች ከላይ ከተጠቀሱት የአማራጭ ግጭት መፍቻ መንገዶች ዉጪ በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚፈቱ ከሆነ ከሁለት ወገኖች አንደኛዉ ተሸናፊ ሌላኛዉ ደግሞ አሸናፊ ይሆናሉ ማለት ነዉ፡፡
- ✓ ከዉይይት ፣ ድርድር እና ከግልግል ዳኝነት ጋር በንጽጽር ሲታይ የፍርድ ቤት ዳኝነት በወጪም ሆነ በቀጣይ በሁለቱ ወገኖች መካከል ሊኖር በሚችል የግንኙነት አይነት አሉታዊ ተፅዕኖ የመፍጠር ዕድል ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ግጭቶችን ወይም አለመግባባቶችን በፍርድ ቤት ዳኝነት መፍታት የመጨረሻ መፍትሄ ነዉ ማለት ነዉ፡፡
- ✓ ነገር ግን በዉይይት ፣ በድርድር ወይም በግልግል ዳኝነት ጉዳዮች የሚያልቁ ከሆነ ሁለቱም ወገኖች እኩል አሻናፊዎች ከመሆናቸዉም በላይ ቀጣይ ማህበራዊ ግንኙነታቸዉ ጤናማ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነዉ፡፡ ይህ ማለት ግን የግልግል ዳኝነት የሚካሄደዉ ከኢትዮጵያ ዉጪ የሚሆን ከሆነ ከወጪም ሆነ ከጊዜ እና በቀጣይ ሊኖር በሚችል ግንኙነት አሉታዊ ተጽእኖ የመኖሩ እድል እጅግ ሰፊ ነዉ፡፡
- ✓ መንግስት እና የዓለም ባንክ ወይም ሌሎች አህጉረዊና ዓለም አቀፋዊ የገንዘብ ተቋማት የመሰሉ የልማት አጋሮች ስምምነቶችን ሲፈራረሙ የግጭት መፍቻ መንገዶችንም በዚያዉ የስምምነት ሰነድ ዉስጥ ያስቀምጣሉ፡፡

- ✓ ፕሮጀክቱ ለማህበረሰቦች በቀጥታ ገንዘብ እንዲተላለፍ የሚጠይቅ ከሆነ እና ገንዘብ ከፋዮች ከማህበረሰቦች ተወካዮች ጋር ዉል የሚዋዋሉ ከሆነም ግጭቶች የሚፈቱባቸው አሰራሮች በዚያዉ ሰነድ ላይ በግልጽ ይቀመጣሉ፡፡

- ✓ በመሆኑም እያንዳንዱ ወገን ግዴታዉን በአግባቡ ካልተወጣ በስምምነቱ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

- ✓ ጉዳዩ ዓለም አቀፋዊ ስምምነት በሚሆንበት ጊዜ በተለይ የግጭት መፍቻ ቦታዎች ወይም ተቋማት መቀመጫ ፕሮግራሙ ከሚካሄድበት ሀገር ዉጪ ይደረጋል፡፡

- ✓ ይህ ደግሞ ተጎጂ ማህበረሰቦችን ወይም መንግስታትን ጥቅም የመጉዳቱ ዕድል ይሰፋል፡፡

- ✓ ምክንያቱም ግጭቶችን በአለም አቀፍ ግጭት ፈቺ አካላት ለመፍታት የሚጠይቀዉ ጊዜ ፣ ዕዉቀት እና ገንዘብ ቀላል አይሆንም፡፡

- ✓ በአጠቃላይ በዓለም አቀፍ የግጭት አፈታት መንገዶች ግጭቶችን መፍታት ሲታሰብ ወጪ ቆጣቢዉንና ልማትን በማይጎዳ መንገድ የሚፈታዉን የግጭት መፍቻ መንገድ መከተል ብልህነት ነው፡፡

- ✓ ስለዚህ መንግስት ለቅሬታ የሚዳርጉ ነገሮች እንዳይፈጠሩ አስፈላጊዉን ቅድመዝግጅት ማድረግ እና ተፈጥረዉም ከሆነ ሁሉንም አካላት የሚያስማማ እና ወጪ ቆጣቢ የእርምት ስራ መስራት አለበት፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ስልካቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ሽልማት ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ ከሚችሉ የቅሬታ ምንጮች 3ቱን ጥቀስ/ሽ፡፡
2. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በአለም አቀፍ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ የፕሮጀክት ተግባሪ ሀገራት ዜጎቸ እና መንግስታት መከተል የሚገባቸዉን ቅድመ ሁኔታዎች በአጭሩ አብራራ/ሪ፡፡
3. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በዓለም አቀፍ መርሆዎች መሰረት መጨረስ ያለዉን ጥቅም አብራራ/ሪ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ15ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የቅሬታ ምንጮች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ. የጥቅም ክፍፍል ፣

ለ. የደን ሀብትን በነጻነት መጠቀም ፣

ሐ. የመሬት ወይም የደን ይዞታ ማረጋገጫ ጉዳይ ፣

መ. ከካርቦን ግብይት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ፣

ሠ. ደኖችን ከማስተዳደር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፤

ረ. ከፕሮግራሙ ጋር የተያያዙ ስራዎችን ለማከናወን ከሚደረግ የበጀት አመዳደብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣

ሰ. የሙስና ጉዳይ ፣

ሸ. የካርቦን ክፍያ የማዘግየት ወይም በዉል መሰረት ያለመክፈል ጉዳይ እና የመሳሰሉ ጉዳዮች ዋና ዋና የቅሬታ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**የ15ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በአለም አቀፍ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ

የፕሮጀክት ተግባሪ ሀገራት ዜጎች እና መንግስታት የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች መከተል አለባቸዉ፡፡

ሀ. ግጭቶችን/አለመግባባቶችን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ዉጪ ባሉ አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች ለመፍታት የበኩላቸዉን ጥረት ማድረግ፡፡

ለ. ግጭቶች/አለመግባባቶች በአማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች የማይፈቱ ሲሆን በሀገር ዉስጥ መከተል የሚገባቸዉን ህጋዊ አካሄዶች በጥንቃቄ በመከተል ለመፍታት ጥረት ማድረግ፡፡

ሐ. የሀገር ዉስጥ የግጭት መፍቻ መንገዶችን ሙሉ በሙሉ አሟጦ መጠቀም እና

መ. በዉል የተመለከቱ የአለም አቀፍ ግጭት መፍቻ መንገዶችን በመከተል በዓለም አቀፍ ደረጃ ዳኝነት ለተሰጠዉ አካል ጉዳዩን በማቅረብ መፍተሄ ማግኘት

**የ15ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን ዓለም አቀፍ መርሆዎችን መሰረት ባደረገ ዉይይት (negotiation)፣ ድርድር (mediation) እና ግልግል ዳኝነት (arbitration) መጨረስ ያለዉ ጥቅም የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ሀ. ከአላስፈላጊ የጊዜና ገንዘብ ወጪ ያድናል፡፡

ለ. ሁለቱም ወገኖች ጉዳያቸዉን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ በማድረግ ለወደፊት የሚኖራቸዉ ግንኙነት ጤናማ እንዲሆን ያግዛል፡፡

ሐ. ዘላቂ ሰላምና መተማመን እንዲኖር ያግዛል፡፡

መ. ሁለቱንም ወገኖች አሸናፊ ያደርጋቸዋል፡፡ ምክንያቱም ያጠፋዉ ወገን ይቅርታን በመጠየቅና በጥፋቱ በመፀፀቱ እንዲሁም በሽማግሌ ውሳኔ መሰረት ተበዳዩን በመካስ የእርቀሰላሙ ተጋሪ ስለሚሆን አሸናፊ ሲሆን ተጎጂዉ ወገን ደግሞ በእልህ ጉዳዩን ከማካረር ይልቅ ለአጥፊዉ ወገን ይቅርታን በመስጠቱ እና በአስታራቂዎች ፊት ከጥፋተኛዉ ወገን ጋር ተቃቅፎ እርቀ-ሰላም በማዉረዱ አሸናፊ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

------------------------------//--------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ የሥርጭት ክፍል 16

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልክቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

## በኢትዮጵያ ያሉ የቅሬታ አፈታት አማራጮች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኋላ፡-

1. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አፈጻጸም ሒደት በሀገር ደረጃ ሊያገለግሉ የሚችሉ የግጭት አፈታት መንገዶችን ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡
2. በፕሮግራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በሀገር ዉስጥ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ መከተል ስለሚገባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
3. ቅሬታዎችን ወጪ ቆጣቢ እና ልማትን በማይጎዳ ሁኔታ መፍታት በሚኖረው ፋይዳ ዙሪያ ጥሩ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

4. ቅሬታዎችን በዉይይት (negotiation) ፣ በድርድር (mediation) እና ግልግል ዳኝነት (arbitration) መጨረስ ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን ይገነዘባሉ፡፡

5. ቅሬታዎችን ከማስተናገድ እና ከመፍታት አንጻር የሀገር ሽማግሌዎች ፣ የሀይማኖት አባቶች እና መንግስት ምን ዓይነት ሚና እንደሚኖራቸው ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ የዓለም አቀፍ ስምምነት ሰነዶችንና ቃል ኪዳኖችን በመፈረም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከግንባር ቀደሞቹ ሀገራት ተርታ ተሰልፋለች፡፡

በአፍሪካ ደረጃ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች እና ከጥንት ጀምሮ የራሷን ነጻነት ያላስደፈረች መሆኗ ለግንባር ቀደምነቷ በታሪክ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

የኢፌዴሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 13(2) ሀገሪቱ የፈረመቻቸዉና የተቀበለቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የቃል ኪዳን ሰነዶች የሀገሪቱ ህጎች አካል እንደሆኑ ያስቀምጣል፡፡

በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለዉጥ ቃልኪዳን ሰነድ ፣ ኪዮቶ የአየር ንብረት ለዉጥ ፕሮቶኮል ፣ ካንኩን የአየር ንብረት ለዉጥ ሰነድ እና ሌሎች ሀገራችን ኢትዮጵያ የፈረመቻቸዉ እና የተቀበለቻቸዉ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና የቃል ኪዳን ሰነዶች የሀገሪቱ ህግ አካል ናቸዉ ማለት ነዉ፡፡

ይህ ማለት ግን ቅሬታዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ ዜጎች ጉዳዮቻቸዉን በሀገራቸዉ የፍትህ እና አስተዳደር አካላት ዘንድ ቀርበዉ መፍታት አይችሉም ማለት አይደለም፡፡

ይልቁንም ቅሬታዎችን በመፍታት ሒደት ውስጥ በሀገር ደረጃ ያሉ የቅሬታ መፍቻ አደረጃጀቶችንና እርከኖችን አሟጦ መጠቀም ግዴታ መሆኑን እነዚህ ሰነዶች ያመለክታሉ፡፡

በሀገር ደረጃ ያሉ የቅሬታ መፍቻ አማራጮችም እንደ ዓለም አቀፉ ሁሉ በሶስት ይከፈላሉ፡፡

እነሱም ዉይይት (negotiation) ፣ ድርድር (mediation) እና የግልግል ዳኝነት (arbitration) ናቸዉ፡፡

በዚህ መሰረት ሁለት ግለሰቦች እርስ በርስ የሚፈጠሩ ያለመግባባቶችን በዉይይት መፍታት ይችላሉ ማለት ነዉ፡፡

በዉይይት የማይፈታ ከሆነ ጉዳዩን በሀገር ሽማግሌዎች/በሀይማኖት አባቶች ወይም በአካባቢዉ ለዚህ ዓላማ ተብሎ በተሰየመ ኮሚቴ አደራዳሪነትና አስታራቂነት በመፍታት ገንዘባቸዉንና

ጊዜያቸዉን ሳያባክኑ ወደ ልማት ስራዎቻቸዉ መመለስ ይችላሉ ማለት ነዉ።

ከላይ በተመለከቱት አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች አለመግባባቶች ካልተፈቱ የግልግል ዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል በሚያስተላልፈው ውሳኔ ቅሬታዎች ሊፈቱ ይላሉ።

ነገር ግን ሦስቱንም የግጭት መፍቻ አማራጮችን ተጠቅመዉ ቅሬታዎች ካልተፈቱ እንደ ጉዳዮቹ ባህሪ ወደ ፍርድ ቤት ፣ አስተዳደራዊ መዋቅሮች፣ ፀረ-ሙስና ፣ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ወይም ጉዳዩን ለመፍታት ስልጣን ወዳላቸው ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች በማመልከት ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጠዉ ማድረግ ይቻላል።

በመሆኑም በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ዝግጅትም ሆነ ትግበራ ምእራፎች እንዲሁም በክፍያ አፈጻጸም ምእራፎች በግለሰቦች ፣ በማህበራት እና በማህበረሰቦች መካከል ቅሬታ የሚነሳ ከሆነ ቅድሚያ የሚሰጠዉ በሀገራችን ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ግጭቶችን ለመፍታት ጥረት ማድረግ ይሆናል ማለት ነዉ።

ይህ ማለት ጉዳዮ በባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ማለቅ የሚችል ከሆነ በባህላቸዉ መሰረት በመዳኘት በጊዜ ወደ ልማት ስራዎቻቸዉ መመለስ ፤ ካልሆነ ግን እንደ ጉዳዩ ባህሪ በፍርድ ቤት የሚያልቅ ከሆነ ወደ ፍርድ ቤት ፣ በአስተዳደራዊ ዉሳኔ የሚፈታ ከሆነ በየደረጃዉ ባሉ የአስተዳደር መዋቅሮች መፍታት ተገቢ ነዉ ማለት ነዉ።

ከፕሮግራሙ ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ቅሬታዎች ዙሪያ ለዜጎች የተቀላጠፈ የቅሬታ አፈታት ሥርዓትን ከመዘርጋት አንፃር ተደራሽ የሆኑ የቅሬታ አፈታት አግባቦች በፌዴራል ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ሴክሬታሪያት በኩል በዝርዝር ተቀርፀው ወጥተዋል።

በክልልም ደረጃ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ያስገቡ የቅሬታ አፈታት ሥርዓቶች በዝርዝር ተዘጋጅተው ስለሚቀርቡ እነዚህን ሥርዓቶች በተገቢው መንገድ መጠቀም ትልቅ ጥቅም ይኖረዋል ማለት ነው።

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን። ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ካርዳቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል። አንድ

መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ግዥ ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያግዙና በዓለምም ሆነ ሀገር ደረጃ ያሉ 3 ዋና ዋና አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶችን ጥቀስ/ሽ፡፡
2. በፕሮግራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በሀገር ዉስጥ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ መከተል ስለሚገባን ቅድመ ሁኔታዎች አብራራ/ሪ፡፡
3. ቅሬታዎችን በዉይይት (negotiation) ፣ በድርድር (mediation) እና ግልግል ዳኝነት (arbitration) መጨረስን በተመለከተ የያንዳንዳቸውን አፈፃፀምና ባህርያት አብራራ/ሪ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

### የ16ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያግዙና በሀገር ደረጃ ያሉ 3 ዋና ዋና የግጭት መፍቻ መንገዶች ዉይይት (negotiation) ፣ ድርድር (mediation) እና የግልግል ዳኝነት (arbitration) ናቸዉ፡፡

### የ16ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ

በፕሮግራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በሀገር ዉስጥ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ መከተል የሚገባን ቅድመ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ. በመጀመሪያ ጉዳዩ በሁለትዮሽ ፊት ለፊት በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረግ ዉይይት (negotiation) ለመጨረስ ጥረት በማድረግ፣

ለ. በዉይይት አለመግባባቱን መፍታት የማይቻል ሲሆን በሶስተኛ ወገን አደራዳሪነት በድርድር (mediation) በመፍታትና በእርቅ መጨረስ እና

ሐ. በድርድር መጨረስ ካልተቻለ ወይም ጉዳዩ ለእርቅ የማይቀርብ ዓይነት እንደ ሙስና እና ሰብዓዊ መብት ጥሰት ዓይነት ጉዳይ ሲሆን በግልግል ዳኝነት (arbitration) መጨረስ ናቸዉ።

**የ16ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

ጉዳዮች በዉይይት (negotiation) የሚፈቱ ከሆነ ሁለት ወገኖች በጠረጴዛ ዙሪያ በሚያደርጉት ዉይይት ይፈታሉ እንጂ ሦስተኛ ሰዉ በመካከላቸዉ በአወያይነትና አስታራቂነት አይገባም። በዉይይት (negotiation) ጊዜ ተግባር ላይ የሚዉል አስገዳጅ የስነስርዓት ቅደም ተከተልም የለም። የሚተላለፉ ዉሳኔዎችም በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ብቻ የሚደረጉ ናቸዉ።

አለመግባባቶች በድርድር (mediation) የሚፈቱ ከሆነ በሁለቱ ወገኖች መሐከል ሶስተኛ ወገን በአደራዳሪነት ጣልቃ ይገባል። ሆኖም የዚህ ሰዉ ሚና ሁለቱን ወገኖች ለማስማማት ጥረት ከማድረግ ባለፈ አስገዳጅ ዉሳኔ የመወሰን ስልጣበን የለዉም። በድርድር (mediation) ጊዜም ተግባር ላይ የሚዉል አስገዳጅ የስነስርዓት ቅደም ተከተል የለም።

ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት (arbitration) የሚያልቁ ከሆነ ጉዳዮቹ የሚመሩት በተጻፈ ሕግ ወይም ዉል መሰረት ነዉ። ጉዳዩን የሚመራዉም በሕግ የግልግል ዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ነዉ። በገላጋይነት ጉዳዩን የሚመለከተዉ አካል የሚወስነዉ ዉሳኔ አስገዳጅ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ እንደሚችል ሁለቱ ተገላጋይ ወገኖች አስቀድመዉ አዉቀዉ የሚስማሙበት ይሆናል። ግልግል ዳኝነቱን የሚሰጠዉ አካል የህግ ባለሙያ እና ስለሕግ በቂ እዉቀት ያለዉ አካል ነዉ።

------------------------------//--------------------------------//---------------------

## ሣምንታዊ ሥርጭት ክፍል 17

**ይህ ኢኒሼቲቭ ፎር ሊቪንግ ኮሚዩኒቲ አክሽን (ኢልካ) ከአርባ ምንጭ ኤፍ ኤም ሬድዮ 90.9 ጋር በመተባበር የሚያቀርብላችሁ በአየር ንብረት ለዉጥ ዙሪያ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ (REDD+) ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና አቅም ግንባታ ዝግጅት ነዉ፡፡**

**አዘጋጆች**
**ደሳለኝ ከበደ ካዛ እና**
**ዳሮት ጉምኣ ጉጌ**

**አቅራቢ**
**-----------------**

**በፕሮግራሙ መጨረሻ በዛሬዉ ፕሮግራማችን የምናቀርባቸዉን መልዕክቶች አስመልከቶ ሽልማት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ መሆኑን ለዉድ አድማጮቻችን በቅድሚያ እያሳወቅን ሁላችሁም ፕሮግራሙን በንቃት በመከታተል በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 ተሳትፎ እንድታደርጉ እንጋብዛለን፡፡**

### በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ትግበራ እና አፈጻጸም ወቅት ሊነሱ የሚችሉ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያገለግሉ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች

የዛሬዉ ፕሮግራም ዓላማ፡-
አድማጮች ከዛሬዉ ፕሮግራም በኂላ፡-

1. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ቅሬታዎች በአካባቢ ደረጃ ያሉ የግጭት መፍቻ መንገዶችን ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡
2. በፕሮገራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በአካባቢ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ መከተል ስለሚገባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
3. በፕሮግራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን ወጪ ቆጣቢ እና ልማትን በማይጎዳ ሁኔታ መፍታት በሚኖረው ፋይዳ ላይ ጥሩ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

4. በፕሮግራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በዉይይት (negotiation) ፣ በድርድር (mediation) እና ግልግል ዳኝነት (arbitration) መጨረስ የሚኖራቸውን ጠንካራ ጎንና ውስንነት ይገነዘባሉ፡፡

5. ቅሬታዎችን ከማስተናገድ እና ከመፍታት አንጻር የሀገር ሽማግሌዎች ፣ የሀይማኖት መሪዎች እና መንግስት በሚኖራቸው ሚና ዙሪያ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡

✓ ሀገራችን ኢትዮጵያ ጠንካራ ፣ በተግባር የተፈተሹ እና ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጡ የቅሬታ አፈታት ስርዓቶች እንዳሏት ግልፅ ነው፡፡

✓ እንግዲህ እነዚህ አሰራሮች መደበኛ እና ኢ-መደበኛ አሰራሮችን ይይዛሉ፡፡

✓ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን አሰራሮች ተከትለው የተቀረፁት የፌደራል REDD+ የቅሬታ መፍቻ ሰነድም ሆነ በክልል ደረጃ የሚዘጋጀዉ ሰነድ ቅሬታዎችን ለመፍታት ቁልፍ መሳሪዎች ናቸዉ፡፡

✓ በፌደራል የተዘጋጀዉም ሆነ በክልል የሚዘጋጀዉ የቅሬታ መፍቻ ሰነዶች ቅሬታዎች በተሳለጠ መልኩ ይፈቱ ዘንድ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያዋቅራሉ፡፡

✓ ለምሳሌ በቀበሌ ደረጃ የቀበሌ ሊቀመንበር ፣ የሚሊሻ ጽ/ቤት ኃላፊ ፣ የሀገር ሽማግሌ ፣ የሀይማኖት መሪ ፣ የአሳታፊ ደን ማህበራት ተወካይ ፣ የሴቶች እና ወጣቶች ተወካይ ፣ የልማት ጣቢያ ሰራተኛ እና ሌሎች አስፈላጊ የሚባሉ አካላት ያሉት ኮሚቴ መቋቋም እንዳለበት በፌደራል ደረጃ የተቀርፀው ሰነድ ያስቀምጣል፡፡

✓ ቅሬታዎች መጀመሪያ ለዚህ ኮሚቴ ቀርበው እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡

✓ በዚህ ኮሚቴ ዉሳኔ መፈታት ካልቻሉ ወደ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም በይግባኝም ሆነ በቀጥታ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት እና ወደ አስተዳደራዊ መፍትሔ ሰጪዎች መቅረብ እንዳለባቸዉና መፈታት እንዳለባቸዉ መመሪያው ላይ ተመልክቷል፡፡

✓ እንደዚሁም በወረዳ ደረጃ ያሉ ቅሬታዎችንና ከቀበሌ በይግባኝ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለመፍታት ይረዳ ዘንድ የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ፣ የፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ ፣ የፀጥታና

አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ ፣ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት ኃላፊ ፣ የአከባቢ ጥበቃና ደን ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ፣ የዉኃ እና ማዕድን ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ እና የፓሊስ ጽ/በቴ ኃላፊን የያዘ ኮሚቴ በወረዳ ደረጃ ይቋቋማል፡፡

- ✓ በመሆኑም ማናቸዉንም ከደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ቅሬታዎች በፌደራል እና በክልል የቅሬታ መፍቻ ሰነዶች ላይ በተቀመጡ አግባቦች ማስኬድ አስፈላጊም አዋጪም ነዉ ማለት ነዉ፡፡

ዉድ አድማጮቻችን፡- የዛሬዉን ፕሮግራማችንን ከማጠናቀቃችን በፊት በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ እንደጠቀስነዉ ሽልማት የሚያስገኙ ጥያቄዎቻችንን እናቀርባለን፡፡ ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መርጠዉ ቀድመዉ ትክክለኛዉን መልስ የሰጡ 3 (ሦስት) አድማጮች በሞባይል ካርዳቸዉ ላይ ለእያንዳንዳቸዉ የ100 (አንድ መቶ ብር) የአየር ሰዓት የሚሞላላቸዉ ይሆናል፡፡ አንድ መላሽ በአንድ ፕሮግራም ከ100 ብር የአየር ሰዓት በላይ ሊሸለም አይችልም፡፡ ለመልሳችሁ በስቱዲዮ ስልክ ቁጥራችን 0468810288 በመደወል በቀጥታ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- መላሾቻችን ተማሪዎች ከሆኑ ሽልማታቸው እንደፍላጎታቸው ወደ መፃሕፍት ግዥ ሊዞርላቸው ይችላል፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን

1. በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ቅሬታዎች በአካባቢ ደረጃ ያሉ የግጭት መፍቻ መንገዶችን ጥቀስ/ሽ፡፡
2. በፕሮገራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በአካባቢ ባሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ መከተል ስለሚገባን ቅድመ ሁኔታዎች አብራራ/ሪ፡፡
3. ቅሬታዎችን በአካባቢ ከማስተናገድ እና ከመፍታት አንጻር የሀገር ሽማግሌዎች ፣ የሀይማኖት መሪዎች እና መንግስት የሚኖራቸውን ሚና አብራራ/ሪ፡፡

## የዕለቱ ጥያቄዎቻችን መልሶች

**የ17ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 1ኛ ጥያቄ መልስ**

በደን መመንጠርና መመናመን የሚመጣን በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮገራም (REDD+) አፈጻጸም ሂደት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ቅሬታዎች በአካባቢ ደረጃ ያሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች፡-

ሀ. ዉይይት (negotiation) ፣

ለ. ድርድር (mediation) እና

ሐ. ግልግል ዳኝነት (arbitration) ናቸዉ፡፡

**የ17ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 2ኛ ጥያቄ መልስ**

በፕሮግራሙ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በዓለም አቀፍ እና በሀገር ደረጃ ተቀባይነትና ተጠቃሚነትን ባገኙና በአከባቢ ደረጃም ጥቅም ላይ ሊዉሉ በሚችሉ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከመፍታት አኳያ መከተል የሚገባን ቅድመ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ. በመጀመሪያ ጉዳዩ በሁለትዮሽ ፊት ለፊት በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረግ ዉይይት (negotiation) ለመጨረስ ጥረት ማድረግ፣

ለ. በዉይይት አለመግባባቱን መፍታት የማይቻል ሲሆን በሶስተኛ ወገን አደራዳሪነት በድርድር (mediation) በመፍታትና በእርቅ መጨረስ እና

ሐ. በድርድር መጨረስ ካልተቻለ በግልግል ዳኝነት (arbitration) መጨረስ ናቸዉ፡፡

እዚህ ጋ ጉዳዩ ለእርቅ የማይቀርብ ዓይነት እንደ ሙስና እና ሰብዓዊ መብት ጥሰት

ዓይነት ጉዳይ ሲሆን በመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት መጨረስ ናቸዉ፡፡

**የ17ኛ ሳምንት የሬድዮ ፕሮግራም 3ኛ ጥያቄ መልስ**

ቅሬታዎችን በአካባቢ ከማስተናገድ እና ከመፍታት አንጻር የሀገር ሽማግሌዎች የሀይማኖት መሪዎች እና መንግስት አስፈላጊዉን ጥንቃቄ እና የጥንቃቄ እርምጃዎች በሙሉ መዉሰድ አለባቸዉ፡፡

- አላስፈላጊ ጫና ፣ መድልዎና ማግለል እንዳይፈጸም እና በዚህም ፍትህ እንዳይዛባ አስፈላጊዉ ጥንቃቄ መወሰድ አለበት፡፡
- የመንግስት ህግ በትክክል መተርጎም እና መፈጸም አለበት ፣
- ለተጎጂዎች ፣ ለጠቋሚዎችና ለማስረጃዎች ህጋዊ ከለላ ሊደረግላቸዉ ይገባል ፤
- ዘላቂ ማህበረሰባዊ ሰላም እና ፍትህ እስኪረጋገጥ ድረስ ጥረት መደረግ አለበት ፣
- ንጹሀን እንዳይጎዱ እና አጥፊዎች እንዳያመልጡ ተገቢዊ የጥንቃቄ እርምጃ መወሰድ አለበት ፣

- ዜጎች ለአላስፈላጊ እንግልት እንዳይዳረጉ እና እንደዚሁም ለገንዘብ ፣ለጊዜ እና ለሞራል ኪሳራ እንዳይዳረጉ ጥንቃቄ መደረግ አለበት ፣
- ተጎጆዎች በተለይ አቅመ ደካሞች ፣ አዛዉንቶች ፣ አካል ጉዳተኞች ፣ ህጻናት ወይም ሴቶች በሚሆኑበት ጊዜ ተገቢዉ ድጋፍ እና ከለላ ሊደረግላቸዉ ይገባል፤ ወዘተ . . .፡፡

እነዚህን ማሟላት ደግሞ የመንግስት፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሐይማኖት መሪዎቸ ድርሻ ይሆናል፡፡

## በሬድዮና በቪዲዮ ግንዛቤ ማዳበሪያ ሥራዎቻችን ዙሪያ ነፃ የሕዝብ አስተያየት

------------------------------//-------------------------------//---------------------